# “መለስ ብዬ ሳየው”
# እውነተኛ ታሪክ ወይስ
# የጥላሸት ቅብ

ከዶ/ር አዲስዓለም ባሌማ

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

1.መግቢያ ........................................................................................................................ 1

2. ዲሞክራሲ..................................................................................................................... 4

3. በዲሞክራሲና በዲሞክራሲ ትግል ያለው የአመለካከት ዝንፈት፣ ..................................... 22

4. የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትና ፌደራሊዝም፣ ................................................... 33

5. ሉዓላዊነትና የአንጃዎች ፖለቲካ፣ ......................................................................... 36

6. ኤርትራ ወይስ አሰብ፣ ..................................................................................... 44

7. ማጠቃለያ፣ ................................................................................................. 53

## 1. መግቢያ

ይህ አጭር ጽሑፍ አቶ ገብሩ አስራት "ሉዓላዊነትና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ ለሕትመት የበቃው መጽሐፍ ተመስርቶ የተዘጋጀ ነው። መጽሓፉን አግኝቼ ካነበብኩት በኋላ የነበረኝ ስሜት በምንም መንገድ "መልስ ወይም አስተያየት" አለመስጠት ነበር። ሆኖም ፈረንጆች እንደሚሉት "silence is tantamount to acceptance" ዝምታ ነገሩን የተቀበሉት ያስመስላል እንዳይሆን ውሱን በሆነ መጠንም ቢሆን አስተያየት ለመስጠት ወሰንኩኝ። ለነገሩ የመጽሐፉ አንድ "ጥሩ" ገፅታው ኋላቀር፣ ፀረ-ሰላምና ፀረ-ለውጥ አስተሳሰቦችን በግልፅና በሰፊው ስላስቀመጠ አስተሳሰቦቹን ለማስተካከል ብሎም ትምህርት ለመውሰድ ዕድል ይሰጣል። መጽሐፉ ብዙ ጉዳዮች አንስቷል። በጣም ብዙ በሆኑት ጉዳዮች ላይም ልዩነት ቢኖረኝም ሁሉም የማልስማማባቸው ጉዳዮች ላይ መጻፉ ሌላ መጽሐፍ ማዘጋጀት ስለሚሆን በተወሰኑት ቁምነገሮች ላይ አተኩሬ ግን ደግሞ መጽሐፉ ያቀረበው የታሪክ ሂደት ይሁን ግምገማ ተቀባይነት እንደሌለው ለማሳየት ነው።

በመጀመሪያ ምንም እንኳን መጽሐፉ ሁለት ንድፈ ሃሳቦች ማለትም "ዲሞክራሲ" እና "ሉዓላዊነት" ከርዕሱ ጀምሮ ይዞ ቢነሳም እነዚህን ንድፈ ሃሳቦች ለመተንተንና መነሻ ለማድረግ አልሞከረም። እንግዲህ እሳቸው የሚያዩበት መነጽር ከመፅሓፍ ውጭ ከሚያራምዱት ፖለቲካና በመጽሐፍ ውስጥ ካሉት ያነሰዋቸው ጉዳዮች አገላለፅ በመነሳት ነው ለማስቀመጥ የምንገደደው። በተደጋጋሚ እንደሚገልፁት የሊበራል ዲሞክራሲ አቀንቃኝ እንደሆኑ ስለሆነ መነፅራቸው ይኸው ንድፈ ሃሳብ ይሆናል ብዬ ወስጃለሁ። ልዓላዊነት ሲሉ ግን ከመጽሐፉ እንደማየው ከኤርትራ ጋር በተደረገው ጦርነትና የአልጀርስ ስምምነት ዙሪያ የሚያጠነጥን ጠበብ ያለ ትርጉም ያለው ነው የሚመስለው።

ስለሆነም የሚመሩበት የፖለቲካ እይታ "ሊበራል ዲሞክራሲ" ነው ስለሚሉ፣ ማንሳት የፈለኩት ይህን አመለካከት ይዘቱ ምንድነው ለልማታችንና የትራንስፎርሜሽን ሩጫችን ምን ትርጉም አለው በሚል ንድፈ ሃሳቡን አጠር ባለ መንገድ ለመተንተን እሞክራለሁ። ሰፊ ንድፈ ሃሳብ ስለሆነ በዚህ አጭር ጽሑፍ ሁሉንም ለመሸፈን ባይቻልም ዋና ዋና ገፅታዎቹ(components) ምንድናቸው በሚልና ለእኛ የሚኖራቸው ትርጉም ለማሳየት ይሞክራል። በተመሳሳይ ሊበራል ዲሞክራሲ ሲነሳ ልማታዊ ዲሞክራሲን ማንሳትና ይዘቱን ማሳየት አስፈላጊ ስለሆነ መጽሐፉም

የምንገመግምበት ንድፈ ሐሳብ በመሆኑ እሱንም በተቻለ መጠን ዋና ዋና ገፅታዎቹ እንዴት አድርጎ የሊብራል ዲሞክራሲ አመለካከት ጉደሎዎቹን እንደሚሞላ፣ በልማትና ለውጥ ሂደት ያለው ሚና በተለይም የመንግሥት የተመረጠና ውጤታማ የሆነ ጣልቃ ገብነት ከሌሎች አገሮች ተሞክሮ ማለትም ያደጉት ምዕራባውያን አገሮችም ጨምሮ ለማየት ይሞከራል፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው የንድፈ ሐሳብ ትንተና ቀጥሎ ዋና ዋና በምላቸው ላይ አስተያየትና ተቃውሞዬንና የተቃውሞዬን መነሻ አስቀምጣለሁ፡፡ በመጀመሪያ በዲሞክራሲና በዲሞክራሲ ትግል ያለውን ዝንፈት በተለያዩ ክፍሎች በተከታታይ ቢገለፅም ሰብሰብ አድርጌ አየዋለሁ፡፡ ዲሞክራሲ በትጥቅ ትግል፣ የዲሞክራሲ ማዕከልነትና ትርጉሙ፣ ሕብረተሰቡ ለዲሞክራሲ ያደረገው ትግል፣ በትግሉ ወቅት ከተነሱት ድርጅቶች ጋር የነበረው ግንኙነት፣ በተለይም እንደ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ህብረት (ኢድህ) ጋር የነበረው ፊልሚያና አስፈላጊነቱ፣ አሁን ያለው የፓርላሜንታዊ ዲሞክራሲ አሰራር፣ የሌሎች አገሮች ተሞክሮ ምንድነው? በእኛስ እንዴት ይሰራል ወዘተ… በዝርዝር ለማቅረብና የመጽሐፉ ስህተት የት ላይ እንደሆነ፣ ለምን እንደሆነ ያሳያል፡፡

በመቀጠልም በብሄሮች፣ ብሄረሰብችና ህዝቦች መብትና ይህን መብት ከማስከበር ረገድ አንዱና ዋነኛው መሳሪያ በሆነው ፌደራሊዝም ላይ ያለው የተዛነፈ አመለካከትም ይዳስሳል፡፡ አቶ ገብሩ የብሄር ብሄረሰቦች ህዝቦች መብት ኢትዮጵያ ውስጥ አልተከበረም ብለው ስለሚነሱ ይህ አባባላቸው ምንኛ የተሳሳተ እንደሆነ በዝርዝር ማሳየት ይጠይቃል፡፡ በተለይም ኢህአዴግ ብሄር ለብሄር፣ ህዝብ ለህዝብ እያጋጨ "የኢትዮጵያ ስሜትን አደብዝዞታል" በብሄሮችና ብሄረሰቦች መሃከል ያለው "ቅራኔ ተካሯል" የሚለው ግምገማ መሰረት የሌለውና ከንቱ ምኞት መሆኑን በዝርዝር ያሳያል፡፡ ከዚሁ ጋር በማያያዝ አቶ ገብሩ "ኢትዮጵያዊነትና የብሄር ብሄረሰቦች መብት አስታርቆ የሚሄድ ፖሊሲ መቅረፅ" የሚሉት አባባል ምንኛ የተሳሳተ መሆኑን ያሳያል፡፡ የብሄር ብሄረሰቦች መብት መከበር የጠንካራ ዲሞክራሲያዊ ኢትዮጵያዊነት መሰረት መሆኑን፣ በመሃከላቸው መሰረታዊ ቅራኔ እንደሌለ በሚገባ ተንትኖ ያስረዳል፡፡

በመቀጠልም አቶ ገብሩና ጓደኞቻቸው ከህወሓት ረግጠው ከወጡ ጀምረው አሁንም የተወሰኑቱ የሚያራምዱትና ቀልብ ይስባል ብለው የሚያስቡት catchy ቃል "ሉዐላዊነት" ነው፡፡ ምንም እንኳን እላይ እንደተገለፀው በንድፈ ሐሳብ ባያስቀምጡትም በንድፈ ሐሳብ መጀመሩ ጠቃሚ ነው ብዬ ስለማምን በአጭሩ አስቀምጠዋለሁ፡፡ ከዛም እሳቸው የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት አልተከበረም የሚሉት ክስ ውሃ እንደማይቋጥር አሳያለሁ፡፡ የአቶ ገብሩ የሉዐላዊነት አመለካከት

ምንኛ ጠባብ አመለካከትና ከኤርትራ ጋር ባለው ድንበር ላይ የታጠረ እንደሆነ፣ የህዝቡ፣ የኢኮኖሚ፣ የፖሊሲ ወዘተ… ሉዐላዊነት የሚሸረሽር አስተሳሰብ እንዳላቸው፡፡ ባነሱት የድንበር ጉዳይም የተምታታና የህዝብን ዘላቂ ጥቅም ማስከበር የማይችል መሆኑን በተገቢው መንገድ አሳያለሁ፡፡ ከዚሁ ጋር በማያያዝም ከኤርትራ ጋር ስለነበረው ሁኔታና አሁን ስላለበት ይሁን ወደፊቱ ምን መምሰል ስላለበት "ከቀረርቶ ወጥተን" በአካባቢው የፖለቲካና ኢኮኖሚ መተሳሰር (integration) አንፃር እንዴት መስራት እንዳለብን ለመጠቆም ይሞከራል፡፡

ሌላው "ቀልብ ሳቢ" አድርገው የሚጠቀሙበት በመጽሓፍም የተጠቀሙበት የአሰብ ጉዳይ ነው፡፡ እንዲያው በደፈናው በታሪክ፣ በዓለም አቀፍ ሕግ ወዘተ… የባህር በር ይገባናል የሚለው ከመፈክር ያላነሰ ፖለቲካ ምን ማለት ነው፡፡ ምን ዓይነት ታሪካዊ ሂደት ነበር፣ ዓለም አቀፍ ሕግ በውል (treaty) ይሁን በተግባርም precedence ምን አለ? እንዴት ነው መፈታት ያለበት? እንዴት ነው የኛን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መስራት ያለብን በሚል ሰፋ አድርጉ ለማየት ሙከራ ይደረጋል፡፡ ቁም ነገሩ በማይሆን ነገር ከመዋተት የሚሆነውን ጠበቅ አድርገን ብንሰራ በልማታችንና በትራንስፎርሜሽን ስራችን ውጤታማ መሆን እንደምንችል ለማስገንዘብ ጥረት ይደረጋል፡፡

በመጨረሻም ይህ ጽሑፍ በግል የተዘጋጀና ሁሉንም ነገር ማካተት ስለማይችል የቀረቡት ጭብጦችና አስተያየቶች በዛ ደረጃ ግምት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ መጽሓፉ በምንም ተአምር ትክክለኛ መስመርና ስትራቴጂዎች አንግቦ፣ ብቁ፣ አታጋይና ውጤታማ የሆነ የትግል ታክቲክ ለይቶ በየጊዜውም በሂደቱ ይበልጥም ከጉድለቱ እየተማረና አመለካከቱን እያጉለበተ ለመጣው የትግራይ ህዝብና ከአጋሮቹም ሆኖ የኢትዮጵያን ህዝብ አታግሎ በጥቁር አፍሪካ ትልቁ ሰራዊት የነበረውን የደርግ መንግሥት አሽመድምዶ ለዚሁ ላለንበት መድረክ እንድንደርስ ጉህ እንዲቀድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረገውን ድርጅት ፍፁም አይገልፀውም፡፡ ሌሎች የመስመርና ስትራቴጂ እንዲሁም የትግል ታክቲክ ስህተት ፈጽመው ተሽመድምደው ደረግን መጣል የትልቅ ተራራ ስዕል ስለው በትንሽ ገመድ መጐተት ነው፣ ፖለቲካና ኤሌክትሪክ በሩቁ ብለው የትግሉን ሰፈር ጥለው ሲሄዱ በተፈጠረው የፖለቲካ ጭለማ ሳይበገር ራሱን ለትግሉና ለለውጥ አዘጋጅቶ ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈለውን ድርጅት በምንም መንገድ አይገልጽም፡፡ ይህ ማለት ህወሓት ምንም ስህተት አልሰራም አይደለም፡፡ እንኳን ትግልን ያክል ከባድና የተወሳሰበ ሂደት፣ በተመቻቸ ሁኔታም ስራ ሲሰራ ስህተቶች ይፈፀማሉ፡፡ ከታች ለማሳየት እንደምሞክረው አንደኛ ህወሓት መሰረታዊ የሆነ የመስመርና የስትራቴጂዎች ስህተት አለመፈፀሙን ከዚህ በተጨማሪ

ረዥምና መራራ የሆነውን ትክክለኛ የትጥቅ ትግል ታክቲክ መምረጡን፣ በየጊዜውም አዲስ ከሚከሰተው ሂደት ይሁን በትግሉ ሂደት ከሚፈጽማቸው ስራዎች በተለይም ከጉድለቱ እየተማረ፣ እየጐለበተ፣ እየተጠናከረ፣ የህዝቡን ድጋፍ እያገኘ፣ የህዝቡ አለኝታ የሆነ ድርጅት መሆኑን  በማነሳቸው ጥቂት ቁምነገሮች ለማሳየትና ለማስገንዘብ ነው፡፡ እዚሁ ላይ አንድ ማንሳት እምፈልገው ቁምነገር ማንም ሰው ሕግን አክብሮ የሚፈልገውን ተናግሮ፣ ጽፎ በነፃና በሰላም የሚኖርበት አገር መፍጠር መቻላችን ምን ያህል ከደርግ ሥርዓት ርቀን መጓዛችን ተጨባጭ ማሳያ መሆኑን ነው፡፡

## 2. ዲሞክራሲ

ከላይ እንደተገለፀው የአቶ ገብሩ መጽሐፍ በዲሞክራሲና ሉዐላዊነት መነጽር የህወሓት/ኢህአዴግ የትጥቅ ትግል ጉዞ እንዲሁም ከደርግ ውድቀት በኋላ የተፈፀሙትን ሥራዎችና የተከሰቱትን ሁኔታዎች ለመገምገም ሞክረዋል፡፡ ችግሩ  አቶ ገብሩ የሚያዩበት የዲሞክራሲና የሉዐላዊነት ንድፈ ሓሳብ መነጽር አስቀምጠው ግምገማ ባለማድረጋቸውና መጽሐፉ ንድፈ ሐሳብ መነሻ አድርገው ስላልጻፉት ንድፈ ሓሳቡን እንደ ንድፈ ሓሳብ፣ በንድፈ ሓሳቡ መነጽር አይተው ያስቀመጡትን ግምገማ እንደ ግምገማ በሚገባ ለይቶ ነቀፌታዊ ግምገማ (critic) ለመስጠት አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ለነገሩ ያን ያህል የትግል ጉዞ ግምገማ ለመገምገም ከንድፈ ሃሳብ አለመነሳት ከፍተኛ ጉድለት ከመሆኑም ባለፈ እውነታን ለመሸፈን ሆን ተብሎ የተሰራ ኃላፊነት የጎደለው ተግባርም ያደርገዋል፡፡ ሆኖም ያነሷዋቸው ነጥቦች ብዙ ቢሆኑም ዋና ዋና ጉዳዮችን በመግቢያው እንደተገለፀው ከንድፈ ሓሳብ መነሻ በማድረግ ማየት አስፈላጊ ስለሆነ እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ፡፡

ዲሞክራሲ በስፋት የተነገረለትና የሚነገርለት፣ ብዙዎች የሚናፍቁት፣ ከናፍቆትም አልፈው ሕይወታቸውን ሳይቀር መስዋእት የሚያደርጉለት ሥርዓት ሲሆን፣ በሰፊው ደግሞ በትርጉሙ፣ በይዘቱና በዓላማው ከፍተኛ ክርክር የሚደረግበትና ልዩነትም የሚያስተናግድ ሥርዓት ነው፡፡ ሕዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ካልሆነ ዲሞክራሲ አይደለም ከሚሉ፣ በውክልና ካልሆነ ቀጥታዊ ተሳትፎ አይሰራም የሚሉ፣ ከዛም ሁለቱም በሚመች መንገድ ማዳቀል ይቻላል የሚሉ፣ በዚህም ክልል ከፍተኛ ልዩነት ያላቸው አመለካከቶች ይነሳሉ፡፡ በሌላ በኩል ዲሞክራሲ ዓላማው መንግሥት በምርጫ መመስረት ብቻ ነው ከሚሉት፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚ ልማት ጥያቄዎችንም ማካተት አለበት እስከሚሉት በውስጡ የሚያቅፍ

ከፍተኛ ክርክርና ልዩነት ያቀፈ ንድፈ ሃሳብም የአስተዳደር ሥርዓትም መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

ይህን የአመለካከት ልዩነት David Collier እና Steven Levitsky ምን ያህል የአመለካከትና የአስተሳሰብ ልዩነት በዓለም ውስጥ እንዳለ በጥናታቸው ለማሳየት ሞክረዋል። በእነሱ ጥናት ከ550 የተለያዩ የዲሞክራሲ ዓይነቶች እንዳሉ ገለፀዋል።[1] ይህ ጥናት እንግዲህ የWinston Churchill "Democracy is the worst form of government except for all those forms that have been tried from time to time." አባባል ያስከትላል። ቸርችል እንዳሉት ዲሞክራሲ አስቸጋሪ ሥርዓት ቢሆንም ከዚህ በፊት በዓለም ከተሞከሩት ሥርዓቶች በጣሙን የተሻለ ስለሆነ በተቻለ መጠን የአብዛኛውን ሕዝብ መብትና ጥቅም የሚያስከብረውን ዓይነት ማጉልበትና በተግባር ላይ ማዋል ነው የሚጠበቅብን። ስለሆነም ምንም እንኳ የተለያዩ አረዳዶች ቢኖሩም በተወሰኑ አጥሮች መታቀፍ የሚችሉ በመሆናቸው ከዚህ በታች አጠር ባለ መልኩ ስለዲሞክራሲ ምንነት ለማየት እንሞክራለን።

## ሀ. ሊብራል ዲሞክራሲ

ሊብራል ዲሞክራሲ የአሁኑ ይዘቱን ከመያዙ በፊት ሊበራሊዝም ያደገው አምባገነን ነገስታትና እነሱን ደግፈው የቆሙትን የወቅቱ (medieval) ተቋማትን በመቃወም ነው። ሊበራሊዚም በአንድ በኩል የነገስታቱና መሳፍንቱ ሥልጣን ለመገደብ፣ በተለይ በሰው ንብረት፣ በሰው አኗኗር፣ ፍላጐትና ስብስብ ላይ የነበራቸው ያልተገደበ ሥልጣን ለመቀነስ ከፍተኛ ርብርብ አድርጓል። ይህ ትግል ቀስ በቀስ ግለሰቦች የፈለጉትን ሃይማኖት፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መንገድ እንዲመርጡ ነፃ መሆን አለባቸው ለሚለው ዶክትሪን መሰረት ሆኗል። በሌላ በኩል ሊበራሊዝም የመንግሥት ሥልጣን ወይም የነገስታቱ ሥልጣን ከፈጣሪ የተሰጠ (Divine or supernatural rights) ሳይሆን በህዝቡ ሉዓላዊ ፍላጐት ላይ መመስረት ይኖርበታል በሚል ነው። ይህ ቀስ በቀስ ወደ የሕዝብ ውክልና አሰራር ብሎም ወደ ዲሞክራሲያዊ ግንባታ ያመራው የትግል ሂደት ነው። ይህም ሆኖ የህዝቡ የመብት ጥያቄዎች የሊበራሊዚም ዋነኛ ትኩረቶች አልነበሩም። ዋናውን የእንቅስቃሴው ትኩረት የመንግሥትን ሥልጣን (State power) መገደብ ነበር። ዲሞክራሲ የመጣው ቆይቶ ነበር። ሲመጣም ሊብራል ዲሞክራሲ ሊብራል ሕብረተሰብ እንዳይፈጠር እንቅፋት ይሆናል ብለው ስላሰቡ እስከዚህም የዲሞክራሲ

[1] David Colleir and Steven Levitsky, "Democracy with Adjectives: Conceptual Innovation in Comparative Research," World Politics 49, no. 3, 1997: 430-51.

መጕልበት ደጋፊዎች አልነበሩም፡፡ ለዚህም ነው ዲሞክራሲ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ለማዳረስ ረዥም ጊዜ የፈጀው፡፡

በዚህም ምክንያት ሊቢራል ዲሞክራሲ ሲጀምር ለባለንብረት ወንዶች የሚያገለግል ነበር፡፡ ከረዥም ጊዜ በኋላ ነው ለአቅመ አዳም ለደረሱ ባለንብረት ላልሆኑ ወንደችም ጭምር የመምረጥ ዕድል የተሰጠው፡፡ የመጀመሪያው የፈረንሳይ ሪፐብሊክ ነበር ለአቅመ አዳም የደረሱ ወንዶች የመምረጥ እድል (Universal male suffrage) በ1792 እ.ኤ.አ የፈቀደው፡፡ ይህ ለብቻ የታየ ክስተት ነበር፡፡ በሌሎቹ ትላልቅ የአውሮፓ አገሮች ግን ከ100 ዓመት በኋላ ነበር ተቀባይነት ማግኘት የቻለው፡፡ በጀርመን በ1871 ዓ.ም.፣ በዩናይትድ ኪንግደም በ1918 /ለሃገራዊ ምርጫ/ እንዲሁም በአሜሪካ በ1870 ዓ.ም. 15ኛው የሕገ-መንግሥቱ ማሻሻያ (the Fifteenth Amendment) የወንዶች የመምረጥ መብት (male suffrage) ቢፈቅድም በደቡባዊ የሃገሪቱ ክፍል እስከ የ1965 ዓ.ም የድምፅ መስጫ መብት ሕግ (Voting Rights Act of 1965) በተሟላ መንገድ ተግባራዊ ሳይሆን ቆይቷል፡፡

የሴቶች መብት ስናነሳ የባሰ ነገር ማየት እንችላለን፡፡ በ1893 ዓ.ም.ኒው ዚላንድ (New Zealand) የሴቶች የመምረጥ መብት ማስከበር ብትጀምረውም በአንዳንድ አውሮፓ አገሮች ከሁለተኛ የዓለም ጦርነት ማብቂያ በኋላ፣ በግሪክ 1952፣ በሲዊዘርላንድ ደግሞ ይባስ ብሎ ለፌደራል ምርጫዎች በ1971 ዓ.ም.ለአባቢያዊ ምርጫዎች (Cantonal elections) ግን እስከ 1990 ዓ.ም. ሴቶች የመምረጥና የመመረጥ መብታቸው ሳይከበር ሲንተት ረዥም ዓመታት ቆይቷል፡፡

ስለዚህ ከላይ እንደተገለፀው ሊበራሊዝም ዲሞክራሲያዊ ይዘቱን ለማጕልበት ምንኛ ፍላጕቱ ውሱን እንደነበርና በከፍተኛ የሕዝብ ትግል እስከቅርብ ጊዜ ሊበራል ዲሞክራሲ የምንለው የዲሞክራሲ ሥርዓት ዓይነት መላውን የኀብረተሰብ ክፍል የማይሸፍን እንደነበር ማየት ይቻላል፡፡ ሊበራል ዲሞክራሲ እንደዚህ ሲያቃትት ባለንበት ዘመን አሁን ያለውን ይዘት ለመያዝ እንደቻለ መገንዘብ ይቻላል፡፡

የሊብራል ዲሞክራሲ ዋነኛዎቹ ይዘቶች ምንድናቸው የሚለው ጥያቄ ስናነሳም የተለያዩ መልሶች እናገኛለን፡፡ ዝቅተኛው አገላለጽ (minimalist concept) የሚባለው Joseph Schumpeter የተጠቀመበት የሊበራል ዲሞክራሲ አገላለጽ ነው፡፡ ዲሞክራሲ ግለሰቦች በውድድር የህዝብን ድምፅ በማግኘት የፖለቲካ ውሳኔዎች ላይ ለመድረስ የሚያገለግል ተቋማዊ

መንገድ (institutional arrangement) ነው በሚል ይገልፀዋል፡፡[1] በመቀጠልም በዲሞክራሲ ዋንኛው የመራጩ ህዝብ ሥራ መንግሥት ማቋቋም ነው ይላል፡፡[2] ይህን ሲያብራራ በጥቅሱ እንደተገለፀው ዲሞክራሲ በተግባር የሕዝብ አገዛዝ እንዳልሆነ፣ ዲሞክራሲ ማለት ምረጡን ብለው የሚቀርቡትን ግለሰቦች የመቀበል ወይ ያለመቀበል መብት እንደሆነና በሌላ አገላለፅ ዲሞክራሲ የፖለቲካኞች አገዛዝ ነው ይለዋል፡፡ ይህ አገላለፅ በጣም ጠባብ አገላለፅ ነው፡፡ ሊበራል ዲሞክራሲን በተገቢው መንገድ አይገልጽም በማለት ከዚህ ቀጥለው ያሉትን ገፅታዎች (components) እንዳሉት Larry Diamond በሰፊው ይገልፃል፡፡ እነዚህም፣ የመንግሥት ሥልጣን በተመረጡ አካላት እጅ ብቻ መኖር እንዳለበት፣ የአስፈፃሚው ሥልጣን በሌሎቹ የመንግሥት ቅርንጫፎች መገደብ እንዳለበት፣ ማንም ሰው ወይም ቡድን የመደራጀትና የመወዳደር መብት መኖር፣ ማንነት የሚገልፁ ማናቸውም የባህል፣ የቋንቋ የሃይማኖት የመግለጽ ወይም የመጠቀም መብት፣ በማህበራት የመደራጀትና የመንቀሳቀስ መብት፣ መረጃ ከተለያዩ ምንጮች የማግኘት መብት፣ ግለሰቦች የእምነት፣ የአስተሳሰብ፣ የውይይት፣ የሕትመት፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና አቤቱታ (petition) የማቅረብ ከፍ ያለ (substantial) መብት መኖር፣ የዜጎች በሕግ ፊት እኩል መሆን፣ ነፃ የዳኝነት ሥርዓት መኖር፣ እንዲሁም የሕግ የበላይነት (the rule of law) መኖር፣ ዜጎች ሕጋዊ ካልሆነ እስር፣ ስደት፣ ሽብር፣ ስቃይ(torture) እንዲሁም በሰው የግል ህይወት አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት ከመንግሥት ብቻ ሳይሆን ከተደራጁ መንግሥታዊ ያልሆኑና ፀረ-መንግሥት ከሆኑ ኃይሎች ጥበቃ እንደሚያገኙ ነው፡፡[3] እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት መብቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ በሕገ መንግሥቱ መቀመጥ እንዳለባቸው አበክሮ ያስረዳል፡፡ እነዚህ ከላይ የተገለፁት መብቶች በየሕገ-መንግሥቱ ቢሰፍሩም ይህን ሁሉ በተሟላ መንገድ ተግባራዊ የሚያደርግ የሊበራል ዲሞክራሲ ሥርዓት እንደሌለ Robert Dahl በሰፊው ያስረዳል፡፡ Robert Dahl እስከአሁን የተሟላ ዲሞክራሲ የሚተገበር አገር ስለሌለ በተወሰነ ደረጃ ተግባራዊ የሚያደርጉትን polyarchy ብሎ ይጠራቸዋል፡፡[4] polyarchy ማለት ደግሞ የብዙሃን አገዛዝ ማለት ነው፡፡

---

1 Schumpeter, Captialism, Socialism and Democracy, 1987: 269.

[2]Ibid, p.273

[3]Diamond, Larry, Developing Democracy Toward Consolidation, 1991: 11-12.

[4]Dahl, polyacrhy, 1971: 4-8; see also Dahl, Democracy and Its Critics, 1989:220-21; and Dahl, Modern Political Analysis, 1991: 72-74.

ዲሞክራሲ ባለበት ደረጃ እንዲሰራ ወደፊትም እየተጠናከረ እንዲሄድ ለዲሞክራሲ የሚበጅ የፖለቲካ ባህል እየገነቡ መሄድ ይጠይቃል፡፡ ብዙ ጊዜ የሚነሱት ጽንፈኝነትን ማስወገድ (moderation)፣ መቻቻል (accommodation)፣ በተቻለ መጠን መተባበርና (cooperation)፣ መደራደር (bargaining) ናቸው፡፡ እነዚህን ልምዶች  በማጐልበት ዲሞክራሲው እንዲጠናከር አብዛኛው ሕዝብ በሥርዓቱ እምነት እንዲኖረውና እንዲሳተፍበት ማድረግ ይቻላል የሚል ነው፡፡ Diamond እንዳለው "Democratic consolidation is most evident and secured when support for democracy is not only unconditional but also widely shared by all major political groups and tendencies".[1] ዳያሞንድ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በሚገባ መንገድ ስር ሰዶ የሚጠናከረው ሁሉም የፖለቲካ ቡድኖችና የሚንሸራሸሩ አመለካከቶች ያለምንም ማወላወል ለሥርዓቱ የተሟላ ድጋፍ ሲሰጡ መሆኑ አበክሮ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ ረገድCivil society ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወትም የሚታወቅ ነገር ነው፡፡

ሊብራል ዲሞክራሲ (main stream) ከሚለው በላይ ሂደው ዲሞክራሲ መስራት (እውን መሆን) ካለበት ሌሎች መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች አሉ ብለው የሚከራከሩ ፀሐፊዎች አሉ፡፡ David Held የሚባለው ፀሐፊ "Democratic autonomy" የሚለውን አስተሳሰብ ያራምዳል፡፡ ይህን ሲገልፀው " without tough social and economic rights, rights with respect to the state could not be fully enjoyed and without state rights new forms of inequality of power, wealth and status could systematically disrupt the implementation of social and economic liberties".[2] ጠንካራ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ያለመኖር የሥልጣን፣ የሃብትና ሕብረተሰባዊ ቦታ ልዩነትን በማስፋት የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ነፃነቶች ተግባራዊ እንዳይሆኑ መሰረታዊ እንቅፋቶች መፈጠራቸው የማይቀር መሆኑን ያስረዳል፡፡

በመቀጠልም ህዝቡ ዲሞክራሲያዊ መብቱን መጠቀም ካለበት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ነፃነቱን ማስተናገድ ይገባል፡፡ ካልሆነ ግን Carl Cohen እንደሚቀጥለው ይላል፡፡ "Where the members of a community suffer from chronic malnutrition and frequent illness, participation in common affairs that is both broad and deep is difficult to maintain. Where the lot of the masses is often that of acute hunger, or where

---

1 Diamond, 1991: 175.

2. Held, Models of Democracy, P. 285.

disease runs rampant, the expectation of any genuine democracy among such masses is naïve".[1] ከላይ እንደገለፀው ረሃብ፣ በሽታና ችግር በነገሰበት ህዝቡ መብቱን ያስከብራል፤ በአገር ጉዳይ በተገቢው መንገድ ይሳተፋል ማለት የዋህነት ነው የሚል ነው፡፡

ከላይ በዝርዝር እንደተገለፀው ሊበራል ዲሞክራሲ ለተለያዩ ሰዎች የተለያየ ትርጉምና ይዘት እንዳለው ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ኮርፖሬት ካፒታሊዝም የበላይነት በያዘበት በጣም በበለፀጉት ሃገራት ያለው ሥርዓት ምንኛ ከንድፈ ሃሳቡም እንደሚጋጭ በርካታ የሥራዓቱ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ Robert Dahl የሚከተለውን ይላል፡፡ "Modern Corporate Capitalism tends to produce inequalities in social and economic resources so great as to bring about severe violations of political equality and hence of the democratic process".[2] በጥቅሱ እንደተገለፀው ሮበርት ዳል ዘመናዊው ኮርፖሬት ካፒታሊዝም በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የሃብት አጠቃቀም ከፍተኛ ልዩነት እንደሚፈጠርና ይህ የተራራቀ የሃብት የአጠቃቀም ልዩነት የሰዎችን የፖለቲካ እኩልነትን እንደሚጐዳና ብሎም በዲሞክራሲ ሂደቱ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለው ይገልፃል፡፡

ስለዚህም ሊበራል ዲሞክራሲ ከሱ ለየት ካሉት የዲሞክራሲ ዓይነቶች ብቻ ሳይሆኑ በውስጡም minmalist ከሚባለው እስከ የማህበራዊና ኢኮኖሚ መብቶች መከበር የሚጠይቁ ንድፈ ሃሳቦች እንዳሉ መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም በሊበራል ዲሞክራሲ አመለካከትም በየጊዜው የለውጥ ሂደት እንዳለ ማየት ይቻላል፡፡ ሊበራል ዲሞክራሲ በአግባቡ በሚሰራባቸው የበለፀጉት ሃገራት በአንዱ ወይም በሌላ መንገድ ለአንዱ ወይም ለሌላኛው የህብረተሰብ ክፍል ጥቅም እንዲሰራ ለማድረግ የሚደረግ ትግል አሁንም እንደቀጠለ ነው፡፡ በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ Francis Fukuyama የሚባል ፀሐፊ የሶሻሊስት ካምፕ መፍረስን ተከትሎ ሊበራል ዲሞክራሲ ዘመን የማይሽረው አስተሳሰብ ሆኗል፡፡ ከእንግዲህ አዳዲስ የተለዩ አስተሳሰቦች የመምጣት ዕድላቸው ጠባብ ነው ያለበት ሁኔታ ነበር፡፡ ከላይ እንዳየነው እንኳን ሌላውን የዓለም ህዝብ አጠቃልሎ ሊብራል ዲሞክራሲ በሚሰራበት የበለፀገ ኢኮኖሚም ቢሆንም በዲሞክራሲ ትርጉምና ይዘት "end of history" የሚባል ነገር አይሰራም፡፡ እንደኛ ባሉ ሃገራት የተሻለ የተባለው ሰፋ ያለ (comprehensive) ትርጉም ያለው ሊበራል ዲሞክራሲ ሊሰራ ይችላል ወይ? ቀጥለን የምናየው ይሆናል፡፡

---

[1]Carl Cohen, Democracy, 1971:109.
[2]Robert A. Dahl, A preface to Economic Democracy, 1985:60

## ለ. ልማታዊ ዲሞክራሲ፣

ከላይ እንደተገለፀው ሊበራል ዲሞክራሲ የዲሞክራሲ ይዘቱ ከብዙ ትግልና ጊዜ ከተላበሰም በኂላ በበለፀጉት አገሮች የነበረው ሂደት ብዙ ውጣ ውረድ እንደነበረው የሚታወቅ ነው። እስከ ሁለተኛ ዓለም ጦርነት ባለው ጊዜ በአውሮፓ እምብርት ባሉት አገሮች እንደተጠበቀው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ባለመምጣቱ በተፈጠረው ቀውስ ፋሺዝም የተስፋፋበትና ዓለም ወደ ሌላ እስከፊ ጦርነት የተማገደችበት ነበር። ከሁለተኛ የዓለም ጦርነት ማብቂያ በኂላ የታችኛው የሕብረተሰብ ክፍል የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች ፈጠው በመምጣታቸው በብዙዎቹ የአውሮፓ አገሮች የማህበራዊ ደህንነት (welfare states) ፖለሲዎች ማራመድ የጀመሩበት ነበር። ከብዙዎቹ የአውሮፓ አገሮች ለየት ባለ መልክም በተለይ በስካንዲኒቪያን አገሮች ሶሻል ዲሞክራሲ የሚባለው ንድፈ ሃሳብ ተግባራዊ ያደረጉበት ሁኔታ ነው የተፈጠረው። የሶሻል ዲሞክራሲ አራማጆች ከሊበራል ዲሞክራሲ ለየት ብለው የሚታዩባቸው መሰረተ ሃሳቦች ከነበሩ አንዱ የመንግሥት በኢኮኖሚው የነበረው የጣልቃ ገብነት መጠን ሲሆን ሌላው በባለሃብቱ፣ በላባደሩ መሪዎችና በመንግሥቱ በተፈጠረ ስምምነት ሥርዓቱ ታችኛውን የህብረተስብ ክፍል ኑሮ በውሱን ደረጃ የሚደግፍበትን አሰራር  የሥርዓቱ አካል አድርገው መገንባታቸው ነበር። ሶሻል ዲሞክራሲ የታችኛውን የሕብረተሰብ ክፍል ጥያቄዎች በማለዘብ የኢንዱስትሪ ሰላምን ለማስጠበቅ የሞከረና በአብዛኛውም የቻለ፣ በሊበራል ዲሞክራሲ ማዕቀፍ የሚታይ ሥርዓት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ሲነሳ የአሁኑ የኒዩ ሊበራሎች ፅንፈኛ አመለካከት ወደ ጐን ለጊዜው ትተን በሊበራሊዝምም መጠኑ ከአገር አገር የሚለያይ ቢሆንም ተቀባይነት የነበረውና ያለመንግሥት ጣልቃ ገብነት ዕድገት ማረጋገጥ ከባድ እንደሆነ ተቀባይነት ያለው ተደርጐ የተወሰደ ነበር። ኒዮ ሊበራሊስቶች ብዙ ጊዜ ሊጠቅሱት የማይፈልጉት የAdam Smith አባባል እንደሚከተለው ማየት ይቻላል።

Adam Smith መንግሥት ሦስት ዋና ዋና ሥራዎች አሉት ብሎ የሚቀጥለውን ያስቀምጣል። “First, the duty of protecting the society from the violence and invasion of other independent societies; secondly, the duty of protecting, as far as possible, every member of the society from the injustice or oppression of every other member of it, or the duty of establishing an exact administration of justice; and, thirdly, the duty of erecting and maintaining certain public works and certain public

institutions which it can never be for the interest of any individual, or small number of individuals, to erect and maintain; because the profit could never repay the expense to any individual or small number of individuals, though it may frequently do much more than repay it to a great society."[1]

በጥቅሱ እንደተገለፀው Adam Smith መንግሥት አንደኛ የሕብረተሰብ ሰላም መጠበቅ፣ ከወረራና ሰላማዊ ኑሮውን ከሚያደናቅፉ ሁኔታዎች መከላከል እንዳለበት ያስቀምጣል። ሁለተኛ ሕብረተሰቡ ውስጥ ፍትህ እንዲነግስ እያንዳንዱ ሰው ሌላውን ሰው እንዳይበድል ኢፍትሐዊ ተግባራት እንዳይፈፀምበት መከላከል ግዴታው እንደሆነ፣ ሦስተኛው ደግሞ መንግሥት ሌላው የሕብረተሰብ አባል ወይም የግል ባለሃብት ከትርፋማነት ማነስ ይሁን ከሌላ መነሻዎች ሊሰራቸው የማይፈልጋቸው ግን ደግሞ ለሕብረተሰቡ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ሥራዎችና ተቋሞች ማቋቋምና ማሰራት ግዴታ እንዳለበት ነው። ይህ አስተሳሰብ እ.ኤ.አ 1776 ዓ.ም በጻፈው የታወቀና በጣም ተጠቃሽ በሆነው መጽሐፍ በግልፅ አስፍሮታል።

ሆኖም ኒዮ ሊበራሊዚም 1970ዎቹ መጨረሻ ተጠናክሮ ከወጣ በኋላ ይህን የመንግሥት ሚና ወደ ጐን በመተው እነሱ ራሳቸው የመጡበትን መንገድ ሌላው እንዳይከተለው በማስገደድ በቀጥታ ይሁን እነሱ በሚቆጣጠሯቸው የዓለም አቀፍ ድርጅቶች አማካኝነት በአፍሪካውያንና ሌሎች ክፍለዓለማት በሚገኙ ድሃ አገሮች የመረጧቸውን ፖሊሲዎች መጫን ጀመሩ። ለውድድርና ለልማት አመቺ የሆኑ የመሰረተ ልማትና የልማት ተቋሞች ማቋቋምና ማስፋፋት ሲገባቸውና የገበያ ክፍተትን (market failures) በተመረጠና ውጤታማ መንገድ እንደመሙላት፣ የአፍሪካ ሃገራት የኪራይ ሰብሳቢነት መንስኤ "የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ነው" በማለት በደካማ መንግሥታቱ ላይ ዘመቱ። Structural adjustment በሚል የመንግሥት ተቋማትን በመሸጥ (privatization) በውጭ ባለሃብቶች እጅ እንዲገቡ ተደረገ። ከዚህም በተጨማሪ Macroeconomic indexes በገበያው መወሰን አለባቸው በሚል የባንክ ወለድ በገበያና በባንኮች ነፃ ውድድር ይወሰን፤ የመንግሥት ባንኮች ይሸጡ፣ የውጭ ባንኮችና አገር በቀል ባንኮች በእኩል ይወዳደሩ፣ የውጭ ምንዛሬ ምንም ቁጥጥር አይደረግበትም (የትም ይሸጥ ይለወጥ)፣ የበጀት ጉድለት አስወግዱ ወዘተ... በማለት ተግባራዊ ለማድረግ በከፍተኛ ግፊት ተንቀሳቀሱ። በመጨረሻ ለልማት የሚያመች ሁኔታ ሳይፈጠር የተደረገው privatization & liberalization ከፍተኛ ቀውስ አስከትሎ፣ በ1980ዎቹ መጨረሻ አክራሪ ፖሊሲዎቻቸውን

[1] Adam Smith, The Wealth of Nations, 2 Vols, 1910, Vol 2:180-81.

ለማለዘብ ቢሞክሩም ውጤቱ ኪራይ ሰብሳቢነት ማጥፋት ወይም ማዳከም ሳይሆን ኪራይ ሰብሳቢነት መልኩን እየለዋወጠ ሰፍቶ እንዲመጣና በፖለቲካውም የዜሮ ድምር ፖለቲካ (zero-sum politics) ተጨምሮበት ብዙ ታዳጊ አገሮች ወደ ቀውስ የገቡበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ አሁንም ቢሆን የቆየውን ጠባሳ ማዳን ስላልተቻለ ወደ አዲሱ ሚሊኒየምም ቀውሱ የቀጠለበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡

ይህ የኒዩሊበራሊስቶች ወንጀል በድሃና ታዳጊ የአፍሪካና የላቲን አሜሪካ አገሮች ብቻ ሳይሆን የበርሊን ግንብ ከፈረሰ በኂላም በምስራቅ አውሮፓ አገሮች በሚያሳፍር መንገድ ፈፅመውታል፡፡ ለምሳሌ በሩሲያ የተፈፀመው በስመ privatization ከፍተኛ ዝርፊያና ሌብነት ነበር፡፡ በChicago School of Economics የተቀነቀነው the Shock Doctrine ትንፋሽ በማይሰጥ መንገድ የነፃ ንግድ ሥርዓት (free trade) ፖሊሲዎች ተግባራዊ የማድረግና ወደ 225,000 የሚሆኑ የመንግሥት ተቋማት እንዲሸጡ ማድረግ ነበር፡፡ በዚህም መሠረት ሩሳያውያን ምን እየተፈፀመ እንዳለ በአግባቡ ሳይገነዘቡ ኩባንያዎቻቸው "በውሰዱልን ዋጋ" ነበር የተቸበቸቡት፡፡ ትንሹን ለማሳየት ያህል Naomi Klein በርካታ አጥኚዎች የጻፉትን እንደሚቀጥለው ታስቀምጠዋለች፡፡ "Forty percent of an oil company comparable in size to France's Total was sold for $88 million (Total's sales in 2006 were $193 billion). Norilsk Nickel, which produced a fifth of the world's nickel, was sold for $170 million — even though its profits alone soon reached $1.5 billion annually. The massive oil company Yukos, which controls more oil than Kuwait, was sold for $309 million; it now earns more than $3 billion in revenue a year. Fifty-one percent of the oil giant Sidanko went for $130 million; just two years later that stake would be valued on the international market at $2.8 billion. A huge weapons factory sold for $3 million, the price of a vacation home in Aspen".[1]

ይህ የተፈፀመው ውንብድና Joseph Stiglitz እንዲህ ይገልፀዋል፡፡ "Only a blitzkrieg approach during the 'window of opportunity' provided by the 'fog of transition' would get the changes made before the population had a chance to organize to protect its previous vested interests."[2] Stiglitz በሩሲያ ላይ የተፈፀመው የአገራቱን

[1] Noami Klein, The Shock Doctrine: The Rise of Disaster Capitalism, 2007: 293.
[2] Stiglitz, Quoted in Klein, 2007:283.

ኢኮኖሚ የመዘረፍ ስራ ሂትለር ምዕራብ አውሮፓ ከወረረበት የጦር ስትራቴጂ ጋር ያመሳስለዋል፡፡ በዚህ ሂደት በሩሲያ ጦርነት ወይም ከፍተኛ ወረርሽኝ ምክንያት ሳይሆን በ1998 ዓ.ም.80 ከመቶ የሩሲያ እርሻዎች ከስረው ተዘጉ፣ ከ70 ሺ በላይ ፋብሪካዎች በራቸው ተቆለፈ፣ ከፍተኛ የሥራ አጥ ሰራዊት ተፈጠረ፡፡ ከድህነት ወለል በታች የነበሩ ህዝቦች በ1989 ዓ.ም. 2 ሚሊዮን ሲሆን ከላይ የተገለፀው እንደተፈፀመ ወደ 74 ሚሊዮን አሻቀበ፡፡ ሌላው የተፈጠረው ሕብረተሰባዊ ቀውስ ለመዘርዘር ሰፊ ጊዜና ብዙ ወረቀት ይጠይቃል፡፡ ይህ የተፈፀመው ሌላ መንገድ ስላልነበረ አይደለም፡፡ ሌሎች በተደራጀና ደረጃ በደረጃ ኢኮኖሚያቸውን ወደ ገበያ መር ኢኮኖሚ ለመቀየር ችለዋል፡፡ ዋና ዓላማው ሩሲያን ማፈራረስ እንደነበር የሚሳት አይደለም፡፡

ከላይ የተዘረዘረው እንዳለ የምስራቅ ኤሽያ አገሮች በተለየ መንገድ ማለትም ልማታዊ በሆነ መንገድ ከፍተኛ ዕድገት ካላቸው አገሮች እኩል ለመሰለፍ በቅተዋል፡፡ ልማታዊ መንግሥት (developmental state) መነሻው ከአውሮፓ ማለትም በ19ኛው ክፍለ ዘመን የታየው የፈረንሳይና የጀርመን ፈጣን እድገት ሲሆን፣ ጃፓኖች ራሳቸው አዳብረው ከተደቆሱበት የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ እስከ 1990ዎቹ አጋማሽ የተጠቀሙበትና ተግባራዊ ያደረጉት የልማት መንገድ ነው፡፡ ይህ መንገድ ከሞላ ጐደል ኮሪያኖችና ታይዋኒዞች ተግባራዊ ያደረጉት ነው፡፡  እነዚህ አገሮች በኢኮኖሚያቸው ውስጥ የነበረውን የገበያ ክፍተት (market failures) ያለ መንግሥት ጣልቃ ገብነትና ልማትን የማቀላጠፍ ስራ ውጭ ሊፈታ እንደማይችል የተገነዘቡ ነበሩ፡፡ እነዚህ አገራት ልማትን የህልውና ጉዳይ አድርገው የወሰዱ፣ ከባለሃብቱ በተነፃፃሪ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ነፃነት ያረጋገጡ፣ ብሎም ህዝቡ ልማታዊ አስተሳሰብ እንዲኖረውና ልማትን እንዲደግፍ ያስቻሉ መንግሥታት መገንባት ችለዋል፡፡ በተደረገው እልህ አስጨራሽ የልማት እንቅስቃሴም የኪራይ ሰብሳቢነት የፖለቲካል ኢኮኖሚ የሰፈነበት ሁኔታ ደረጃ በደረጃ ለመቀየር በአንድ በኩል ለልማት ማነቆ የሆኑትን የገበያ ጉድለቶች በተመረጡና ውጤታማ በሆኑ ጣልቃ ገብነት በሂደት በማስወገድ በሌላ በኩል ደግሞ ከልማታዊነትና ከውድድር ውጭ መበልፀግ እንደማይቻል በተግባር በማሳየትና በአመለካከትም ገዥ አስተሳሰብ እንዲሆን በመስራት ተአምር የሚባል ዕድገት ማስገኘታቸው ለሌላው የዓለም ክፍል ሕዝብ ከፍተኛ ትምህርት የሚሰጥ መንገድ ነው፡፡

ሌላው የሚነሳው የህዝብ ተሳትፎ ጉዳይ ነው፡፡ ሊበራል ዲሞክራሲ ህዝቡ ምርጫ በደረሰ ቁጥር ወጥቶ ከመረጠና መንግሥት ካቋቋመ ከዛ በላይ ከህዝቡ የሚጠየቅ ነገር አይኖርም ብሎ ያስቀምጣል፡፡ በተግባርም የሚታየው ይህ ነው፡፡ ይህን ስናነሳ Rousseau ስለእንግሊዝ

ዲሞክራሲ ያለውን ያስታውሰናል፡፡ “The English people believes itself to be free, it is gravely mistaken; it is free only during the election of Members of Parliament, as soon as the members are elected, the people are enslave; it is nothing”. ይላል[1]፡፡ በጥቅሱ እንደተገለፀው የኢንግሊዝ ህዝቦች ነፃ ነን ብለው ቢያስቡም ነፃ አይደሉም፤ ነፃ የሚሆኑት በምርጫ ወቅት ብቻ ነው ይላል፡፡ እንግዲህ Rousseau ሓቀኛ ዲሞክራሲ ቀጥተኛ ተሳትፎ ሲኖር ነው ለማለት ያለው ነው፡፡ ይህ ባለንበት ዘመን በሁሉም ደረጃዎች ቀጥተኛ ተሳትፎ ማድረግ የማይታሰብ ነው፡፡ ሆኖም እንደነ Carol Pateman የመሳሰሉ በውክልና የተቋቋሙ የመንግሥት ኢንስቲቱሺኖች ብቻ ሳይሆን ህዝቡ በሚያመች መንገድና በታችኛው የመስተዳደር እርከንና ኮሙኒቲ ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርግ ማመቻቸት ጠቃሚ ነው ይላሉ፡፡[2] ይህ ልማታዊ ዲሞክራሲ ከሚለው ማለትም ህዝቡ በተቻለ መጠን በልማቱና ማህበራዊ ይሁን አስተዳደራዊ ጉዳዮቹ በተለይ በታችኛው እርከንና አመቺ በሆነ መንገድ ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆን ያበረታታል፡፡ ይህ ተሳትፎ ልማቱንና ዲሞክራሲያዊ መብቱን በማስከበር ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል የሚል እምነት አለው፡፡ በተግባርም በተቻለ መጠን ለመፈፀም ከፍተኛ ርብርብ ይደረጋል፡፡

ልማታዊ ዲሞክራሲ የህዝብን ተሳትፎ ወሳኝነት ለማረጋገጥ በተለይም ብዙህነት መገለጫው በሆነ አገር የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀማል፡፡ አንዱ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ራሳቸው በራሳቸው የሚያስተዳድሩበት ብሎም በሕገ መንግሥታዊ ተሳትፎ የጋራ መንግሥት የሚመሰርቱበት የፌዴራል ሥርዓት ነው፡፡ የፌዴራል ሥርዓት የህዝቡን ዲሞክራሲያዊ መብትና ተሳትፎ በማጠናከር ወደር የሌለው ሚና ይጫወታል፡፡ እንደሚታወቀው ዲሞክራሲ ብቻውን በህብረ ብሄራዊ አገር የተለያዩ ህዝቦችን ተሳትፎ በአግባቡ ማስተናገድ አይችልም፡፡ ዲሞክራሲው በፌደራሊዝም ሲደገፍ ነው ይህን ተሳትፎ መዋቅራዊ መሠረት (institutionalized) እንዲኖረው የሚያደርገው፡፡ ለዚህ ነው Diamond “Federalism serves a valuable role in strengthening democracy by institutionalizing decentralization and thus preserving the autonomy of regional and local governments”.3 በጥቅሱ መሰረት ፌዴራሊዝም ያልተማከለ አስተዳደርን መዋቅራዊ አቋም እንዲኖረው ማለትም

---

[1] Jean-Jacques Rousseau Quoted in Robert A. Dahl, Democracy and Its Critics, 1989: 226.
[2] Carole Pateman, Participation and Democratic Theory, 1970: 42-43.
3. Diamond, Developing Democracy, 1991:151.

የክልሎችና የአካባቢ መንግሥታት በነፃነት ራስን በራስ የማስተዳደርን ሥልጣን ቀጣይነት በማረጋገጥ ዲሞክራሲ ይበልጥ እንዲጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የConsociational Democracy ግብዓቶችን በመጠቀም የህዝቡን እኩል ተሳትፎ በተለይ ደግሞ የአነስተኛ ቁጥር ያላቸው ህዝቦች በበቂ የመደመጥና የመሳተፍ መብት ማረጋገጥ ይችላል፡፡ Consociational Democracy በሚገለፅባቸው አራት መሰረታዊ አቋሞች (principles) ማለት grand coalition, mutual veto, proportionality, and segmental autonomy ብዙህነትን ይበልጥ የሚያስተናግድበትን ሁኔታ ይፈጠራል፡፡[1] ለምሳሌ በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ሰፋ ያሉ የብሔር ተዋፅኦና የትምህርት ዝግጁነትና ችሎታ (merit) ማዕከል ያደረገ የካቢኔ ምስረታ፣ እያንዳንዱ ብሔር ብሄረሰብና ህዝብ የራሱን መስተዳደር የመመስረት፣ ሕገ-መንግሥቱን ለማሻሻል ይሁን አንቀፆች ለመለወጥ የአነስተኛ ህዝቦች ድምፅ ታሳቢ በማድረግ መቀረፁና በውክልናም ረገድ እያንዳንዱ አነስተኛ ህዝብ (minority) ከ10 ሺ ህዝብ የሚሆን ካለው በተወካዮች ምክር ቤት እንዲወከል (22 መቀመጫዎች በአሁኑ ወቅት ለአነስተኛ ህዝቦች የተደለደሉ መኖራቸው)፤ በፌዴሬሽን ምክር ቤትም እንደ ህዝብ ውክልና እንዲያገኝ የመሳሰሉት ይበልጥ ዲሞክራሲ እንደ የብዙሃን አገዛዝ ማስተናገድ የሚሳነውን የአነስተኛ ህዝቦች የተሳትፎና የመደመጥ መብት በፌዴራሊዝምና በConsociational Democracy መሰረተ-ሃሳቦች በማስተናገድ በተሻለ ዲሞክራሲው በፅኑ መሠረት እንዲመሰረት ያደርገዋል፡፡

ልማታዊ ዲሞክራሲ ከላይ እንደተገለፀው ሊብራል ዲሞክራሲ የሚያቀርበው የግለሰብ መብት ወስዶ የሚጐድለውን የቡድን መብቶች በመጨመርና አስፈላጊ የሆኑ ተቋማዊ ድጋፎችን በማካተት ህዝቡ እንደግለሰብም እንደ ቡድንም መብቶቹ የሚከበርበት፣ ተሳትፎው በየጊዜው እየላቀ የሚሄድበት ሁኔታ ነው የሚፈጥረው፡፡ ከዚህ ውጭ ሌላ ትርጉም ለመስጠት መሞከር አለማወቅ ወይም ሆን ብሎ ለማደናገር መሞከር ይሆናል፡፡

---

[1] See Lijphart “Consociation and Federation”, 1979: 500; Lijphart, Democracy in plural societies: A comparative exploration, 1980:25; Lijphart, “The puzzle of Indian Democracy. A Consociational Interpretation,” American Poltical Science Review, 1996, 90,2, p.258-268.

ከላይ የተገለፀው እንዳለ ሆኖ ግን ዲሞክራሲ እንዲጐለብትና የዲሞክራሲ መዋቅሮች እየተጠናከሩና ሥርዓቱ በፅኑ መሠረት እንዲቆም ከተፈለገ የሚካሄደው የፖለቲካ ውድድርና ጨዋታ ሥርዓቱ በሚፈቅደው ክልል ብቻ መሆን አለበት፡፡ በሕግና ከሕግ ውጭ እያጣቀሱ የፖለቲካ ጨዋታ ማካሄድ ሥርዓቱ በፅኑ መሠረት እንዳይገነባ ያደርገዋል፡፡ Diamond እንዳለው “Democracy can be consolidated only when no significant collective actors challenge the legitimacy of democratic institutions or regularly violate its constitutional norms, procedures, and laws”.[1] ይህን አባባል በማጠናከር Juan Linz and Alfred Stepan የተባሉ የታወቁ ፖለቲካል ሳይንቲስቶች የሚከተለውን ይላሉ፡፡ “Consolidated democracy… attitudinally, democracy becomes the only game in town when, even in the face of severe political and economic crises, the overwhelming majority of the people believe that any further political change must emerge from within the parameters of democratic procedures”.[2]

ስለዚህም ሥርዓቱ የሚጠናከረው ችግር እንኳን ቢያጋጥም ሥርዓቱ በሚፈቅደው መንገድ ትግል ሲካሄድ ነው፡፡ ሥርዓቱ በሚፈቅደው ማዕቀፍ ውስጥ ብቻ መንቀሳቀስ እንደብቸኛ አማራጭ አብዛኛው ህዝብ በአመለካከት ሲቀበልና ይህንኑ ተግባራዊ ማድረግ ሲችል ነው፡፡ የሕግ የበላይነት ማክበርና በሕግና በሕግ ብቻ መጫወት ፋይዳው ለሁሉም ተዋናዮች በትልቁ ደግሞ የሥርዓቱ ባለቤት ለሆነው ህዝብ ነው የሚለው ሁሉም ሊገነዘበው የሚገባ ከፍተኛ ቁምነገር ነው፡፡

ልማታዊ ዲሞክራሲ በዲሞክራሲው ገጽታው እንዳየነው ሁሉ በልማታዊ ገጽታውም ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ኒዮ ሊበራሊዝም የድሮው ሊበራሊዝም ይቀበለው የነበረው ጠቃሚ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት አሽቀንጥሮ ጥሎ መንግሥት ከዘበኝነት የተሻለ ሚና ሳይሰጠው እንደቀረና የሁሉ ችግር መነሻ መንግሥት አድርጐ በማየቱ ምን ያህል በታዳጊ አገሮች ከፍተኛ ችግር እንዳስከተለ ተጠቅሷል፡፡

---

1Diamond, Developing Democracy, 1999:67.

[2] Juan J. Linz and Alfred Stepan. “Toward Consolidated Democracies”,In Diamond et al. Conslidating The Third Wave Democracies, 1997:15.

እኒሁ የዘመኑ የበለፀጉት አገሮች አሁን ካሉበት ደረጃ ለመድረስ መንግሥቶቻቸው ከፍተኛ ሚና ሲጫወቱ ነበር ብቻ ሳይሆን የተፎካካሪ አገር ተመሳሳይ ምርት ወደ አገራቸው እንዳይገባ በራቸውን ቀርቅረው ነው የሰሩት። መንግሥታት ወሳኝ የኢኮኖሚ ክፍሎች ተቆጣጥረው፣ የinfant industry የመከላከል ፖሊሲዎች ተግባራዊ አድርገው ነው እዚህ የደረሱት። Friedrich List እንግሊዝ እንዴት infant ኢንዱስትሪዎችዋን ከገቢ ምርቶች ተከላክላ እንዳሳደገቻቸው በሰፊው ያትታል። አሜሪካም በተመሳሳይ መንገድ በሰፊው ሰርታለች። እንዲያውም Paul Bairoch አሜሪካን "The Mother Country and bastion of modern protectionism" ብሏታል።[1] ጀርመንም ሌሎች የሰሜን አውሮፓ አገሮችም የተከተሉት ይሄው ነው። ሌኒን "Commanding heights of the economy" መቆጣጠር የሚለው አባባል ስለተጠቀመ ይህ በሶሻሊስት አገሮች ብቻ የሚፈፀም የኢኮኖሚ ፖሊሲ ነበር ማለት አይደለም። ለነገሩ ሌኒንም ቢሆን በኋላ ቀር ኢኮኖሚ ተይዞ በቀጥታ ሶሻሊዝም መገንባት አይቻልም። ስለሆነም አዲስ ኢኮኖሚ ፖሊሲ (New Economic Policy) የሚባለውን በማዘጋጀት ካፒታሊዝም ቀድሞ መገንባት አለበት ሲል የተጠቀመበት አካሄድ ነው። ያደጉት የምዕራብ አገሮችም ለልማት ጠቃሚዎች ያልዋቸውን ሴክተሮች እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ይቆጣጠሩዋቸው ነበር። አሁንም ጨርሰው ወጥተዋል ማለት አይቻልም።

በቴሌኮም፣ በመብራት፣ በባንኮች፣ በትራንስፖርት እንዲሁም አንዳንድ እንደየሃገሩ ሁኔታ ከፍተኛ ሚና አላቸው በሚልዋቸው ሴክተሮች controlling stake (20% እና ከዛ በላይ ባለቤትነት ሲኖር) አላቸው። ለምሳሌ የጀርመን መንግሥት Commerzbank የተባለውን የጀርመን ሁለተኛው ትልቁ ባንክ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ከ25% በላይ ይቆጣጠራል። የLower-Saxony የክልል መንግሥት በPorsche-Volkswagen ከ20% በላይ ድርሻ አለው። የFinland መንግሥት በStora Enso ትልቁ የዓለም የወረቀት ፋብሪካ ከ25% በላይ ድርሻ አለው። Electricity of France (EDF) ከዓለም ትልቁ የሃይል አመንጪና አከፋፋይ፣ ከ120 Gigawatts የሚያመነጨውና የሚያከፋፍለው ከ65.2 Billion Euro ገቢ ያለው ኩባንያ የፈረንሳይ መንግሥት ነው። በጣልያንም ENEL የተባለው የኤሌክትሪክ አመንጪና አከፋፋይ ኩባንያ እስከ 1999 ዓ.ም. የመንግሥት ሆኖ ቆይቶ ሽያጭ ከተደረገ በኋላም አሁን 25.5% የኩባንያው share መንግሥት ይቆጣጠረዋል። የኔዘርላንድስ መንግሥት ABN AMRO Bank N.V. ማለትም 404.7 Billion Euro ንብረት ያለው ባንክ ባለቤት ነው። የነፃ

[1] Paul Bauroch quoted in Ha-Joon Chang, kicking Away the Ladder, 2003: 24-25.

ገበያ ዋናዎቹ ቁሶች እንግሊዞች፣ በጠቅላይ ሚኒስትር ታቸር በሰፊው የመንግሥት ንብረቶች ቢሸጡም በ1980ዎቹ እስኪሸጡ ድረስ ለልማት ሲጠቀሙባቸው ነበር። አሁንም ቢሆን የባቡርና አብዛኛው የትራንስፖርት አገልግሎት በመንግሥት ስር ይገኛል። የሚገርመው ግን የእንግሊዝ መንግሥት ትናንሽና መካከለኛ ተቋማትን (SMEs) ለመደገፍና ፋይናንስ ለማቅረብ British Business Bank plc አቋቁሞ እየሰራ ይገኛል። ብዙ ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል። ቁምነገሩ መንግሥታት በግል ባለሃብቱ ያልተሞላና ለልማት አስፈላጊ የሚሏቸውን ወይም ለልማቱ ቅልጥፍና መንግሥት የበለጠ አገልግሎት የሚሰጥበትን ሴክተር ለይቶ ቢቆጣጠርና ለልማት ቢጠቀምበት ሃጥያት እንዳይደለ ነው።

ከላይ የተጠቀሰው በኩባንያ ባለቤትነት ያለው ሁኔታ ነው። ከዛ በላቀ ደረጃ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት የታየው 2008 ዓ.ም. ባጋጠመው የፋይናንስና የኢኮኖሚ ከፍተኛ ቀውስ ነው። በቤት ገዥዎች ገበያውን ያልተከተለ ብድር (subprime mortgages) የጀመረው ቀውስ ጠቅላላውን አሜሪካ፣ ከዛም የበለፀጉትን አገሮች ብሎም ለድሃዎቹ አገሮችም ጭምር አስቸጋሪ የሆነ ሁኔታ የፈጠረ ቀውስ ነበር። በወቅቱ የአሜሪካው ፕሬዝዳንት George W. Bush በTroubled Asset Relief Program (TARP) አማካኝነት እስከ $700 ቢሊዮን ዶላር የተበላሹትን ብድሮች መንግሥት በመግዛት ባንኮች እርስ በእርስ መበዳደር እንዲቀጥሉ የተደረገው የህዝብ ገንዘብን በጣም ውሱን ለሆኑ ባንኮችና የእነሱ ባለቤት የሆኑትን ባለሃብቶች ከገቡበት አዘቅት እንዲወጡ ድጋፍ ያገኙበት ነው። ከዚህ የተፈቀደው ከፍተኛ ገንዘብ ዋናዎቹ ባንኮች ማለትም እነ Citigroup, Bank of America, JP Morgan Chase, Wells Fargo, Goldman Sachs, Morgan Stanley, PNC Financial, US Bancorp, GMAC, Capital one, Regions Financial, American Express, Bank of New York Mellon, State Street Bank እና Discover Financial ተጠቃሚ ሆነዋል። ከእነዚህ በተጨማሪ እነ American International Group (AIG), General Motors and Chrysler የተባሉ የመጀመሪያው በዓለም ትልቁ የኢንሹራንስ ኩባንያ ቀጥለው ያሉት ሁለቱ ደግሞ መኪና ሰሪዎች ከውድቀት ፕሮግራሙ ታድነዋቸዋል። Fannie Mae እና Freddie Mac የተባሉት የቤት መግዣ አበዳሪዎችም የተበላሸው የቤት ብድር መንግሥት ገዝቶ የቤቱ ሴክተር ጨርሶ ወደ ከፋ አዘቅት እንዳይገባ አዲስ በርካታ ገንዘብ አቅርቦ ከውድቀት እንዲድኑ አድርጓል። ይህ የአሜሪካ መንግሥት ካደረገው የጣልቃ ገብነት ጥቂቶቹ ምሳሌዎች ናቸው። በእንግሊዝም መንግሥት እንዲሁ ከ£500 billion (ፓውንድ) ባንኮችና ኢኮኖሚው ከመናድ

ለመከላከል (rescue package) በብድርና በዋስትና(guarantee) ያዘጋጀበትና ጣልቃ የገባበት ሁኔታ ነበር፡፡ በሚበዙት የአውሮፓ አገሮች ብቻ ሳይሆን የቻይናና ጃፓንም መንግሥታት ሳይቀር ያራደ ስለነበር ሁሉም መስራት የሚችለውን የሰራበት ሁኔታ ነበር፡፡ አውሮፓ አሁንም ሳይቀር ከዛ ያጋጠማት ቀውስ ተላቃ አልወጣችም፡፡[1]

ጥያቄው ለምን ታድያ እነዚህ መንግሥታት የታዳጊ አገሮች መንግሥታት "ለዘበኝነት ብቻ" የሚመኟቸው የሚለው ነገር እነሱ ያለፉበት መንገድ አሁንም ጨርሰው ያልተውት ስራ እንዳይሰራ የሚከላከሉት አንድም ገዥዎቹ የእነሱ ባለሃብቶች ስለሆኑ በዘረፋው ለመሳተፍ ሌላው ገፅታው ደግሞ ተፎካካሪን የመቀነስ አባዜ ከመሆን አይዘልም፡፡ እዚህ ላይ Friedrich List በ1885 ዓ.ም ባሳተመው መጽሐፍ ያለውን መጥቀስ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

- List argues: "It is a very common device that when anyone has attained the summit of greatness, he kicks away the ladder by which he has climbed up, in order to deprive others the means of climbing up after him.. Any nation which by means of protective duties and restrictions on navigation has raised her manufacturing power and her navigation to such a degree of development that no other nation can sustain free competition with her, can do nothing wiser than to throw away these ladders of her greatness, to preach to other nations the benefits of free trade, and to declare in pertinent tones that she has hitherto wandered in the paths of error; and has now for the first time succeeded in discovering the truth". [2]

በዚሁ ጥቅስ List አንደኛ የዕድገት መሰላሉን ከፍ ብሎ ወጥቶ ያደገ አገር ሌሎች ሃገራት የሱን መንገድ ተከትለው እንዳያድጉ ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ የተለመደ መሆኑ፣ ሁለተኛ

---

[1] የተፈጠረው ቀውስና የተፈፀመው የመንግሥት ጣልቃ ገብነት በዝርዝር ለማየት፣

- Henry M. Paulson, Jr. On the Brink: Inside the Race to Stop the Collapse of the Global Financial System, 2010.
- Timothy F. Geithner, Stress Test: Reflections on Financial Crisis, 2014.
- Andrew R. Sorkin. Too Big to Fail, 2010.

[2] Friedrich List, The National System of Political Economy,1885, pp. 295-6.

በሩን ጥርቅም አድርጐ ዘግቶ በማምረቻ ኢንዱስትሪውም በባህር ትራንስፖርትም ሌላ አገር ሊወዳደረው ወደማይችልበት ደረጃ ከደረሰ በኋላ ከዚህ በፊት የሰራሁት ስህተት ነው። ከተገቢው መንገድ ወጥቼ ነበር፣ አሁን ግን እውነቱን አውቄ ተመልሻለሁ። ስለሆነም ለሁላችን የሚጠቅመን ነፃ ገበያ ነው ብሎ ወደ መስበክ ይገባል። ሊስት እንዳለው በ19ኛው ክፍለ ዘመን ብቻ ሳይሆን በ21ኛው ክፍለ ዘመን የተለመደ ተግባር ሆኖ በየቀኑ እየተባለ እየተነገረለትና እየተፈፀመ ይገኛል።

የኛዎቹ ተቃዋሚዎችስ ለምንድነው የእነዚህን ፍላጐት በጩሀት የሚያስተጋቡት ቢባል አንዱ አለማወቅ ሊባል ይችላል በአብዛኛው ግን የአገልጋይ ሚና (subservient role) ለመጫወት ነው። በ5ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ የፓርቲዎች ክርክር "ይህ ይሸጥ ያ ይደገም" ሲሉ በጣም ይገርም ነበር። አንዳንድ ጊዜ ፈረንጆች እንደሚሉት ከጳጳሱ የበለጠ ካቶሊኮች (More Catholic than the Pope) የሆኑ እስኪመስሉ ድረስ ሲንቀሳቀሱበት ይታያል። አቶ ገብሩ ደግሞ "የመንግሥት ጣልቃ ገብነትን አልቃወምም ግን commanding heights መቆጣጠር የለበትም" ሲሉ ተደምጠዋል። አቶ ገብሩ "commanding heights" የሚባለው እንደየሃገሩ ይለያያል። ሃገሪትዋ ልማትን ለማቀላጠፍ ይጠቅመኛል የምትላቸው ሴክተሮች ናቸው። ባንክ፣ ኮሚኒኬሽን፣ ትራንስፖርት፣ ኢነርጂ ወዘተ… ናቸው። ከዚህ ውጭ መንግሥት ሆቴል፣ ሬስቶራንት ወይም የሳሙና ፋብሪካ ቢቆጣጠር ምኑን የልማት ለውጥ ያመጣል? ባይሆን የግል ባለሃብቱን ቦታ ነው የሚጋፋው። ስለሆነም ደግሞ አቶ ገብሩ ከ"commanding heights" ውጭ ሲሉ ምን እንደሚሉ ለራሳቸውም ግልፅ የሆነላቸው አይመስለኝም።

ስለሆነም ልማታዊ ዲሞክራሲ የሚለውን በአግባቡ መረዳት ይጠይቃል። መንግሥት ለልማት አስፈላጊ በሆኑ የግል ባለሃብቱ ፍላጐቱም አቅምም በሌለባቸውና በተመረጡ ሴክተሮች ጣልቃ ይገባል ነው። እነዚህ ሴክተሮች በኢኮኖሚው እንደድልድይ ሆነው የሚያገለግሉ የልማት መሳሪያዎች ይሆናሉ። በሌላ መንገድም በመንግሥት እጅ ያሉት የቴሌኮም፣ የሃይል የማስተላለፍና የማከፋፈል ሴክተሮች (transmition and distribution sectors)፣ የባንኩ ሴክተርም ከውጭ ባለሃብቶች ራቅ ብሎ ይቆያል ወዘተ… የመሳሰሉት አሁን ለልማታችን ቁልፍ ሚና የሚጫወቱት የኢኮኖሚ ሴክተሮች ለፈጣን የልማት ግንባታችን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ስላላቸው እስከተቻለ ባሉበት ይቆያሉ ነው። እንግዲህ መለኪያው ልማትና ለልማት ያላቸው አስተዋፅኦ ነው። ይህ ነው የልማታዊ ዲሞክራሲ

የኢኮኖሚ ፖሊሲ ገፅታ። ሶስቱ የልማት ሃይሎች የምንላቸው ማለትም ህዝቡ፣ የግል ባለሃብቱና መንግሥት በቅንጅትም በተናጠልም ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ተደጋግሞ ተገልጿል። በተለይ የግል ባለሃብቱ በኢንዱስትሪ ልማት ዋነኛ ሃይል ስለሆነ መደገፍና ሁኔታዎችን ከመንገድ ወጥቶም ቢሆን ማመቻቸት የልማታዊ መንግሥት ተግባር ነው።

በኢትዮጵያ እድገትና ትራንስፎርሜሽን ማረጋገጥ አለብን ስንል ቀልጣፋ ልማት ያስገኙትን አገሮች ተሞክሮ መውሰድና ከአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ተግባራዊ ማድረግ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከእነሱ የሚለየን ከፍተኛ ቁም ነገር እንዳለም መገንዘብ ያስፈልጋል። ከላይ እንደተገለፀው ልማታዊ መንግሥት እንዲኖረን ሲፈለግ ከምስራቅ ኤሽያ አገሮች በተለየ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ራሱን የቻለ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው። ስለሆነም በኢትዮጵያ መኖር የሚችለው ሥርዓት ልማታዊ ዲሞክራሲ ነው የምንለው ለዚሁ ነው።

ልማታዊ ዲሞክራሲ ከፍ ብሎ የተገለፀውን Larry Diamond የዘረዘራቸውን በተለይ በግለሰብ መብት ላይ የሚያጠነጥኑትን የዲሞክራሲ ገፅታዎች (components) ወስዶ እነሱ ግን እንደኛ በመሰለ የብዙ ብሄር ብሄረሰብና ህዝቦችና የተለያዩ ሃይማኖቶች ያሉበት አገር የቡድን መብቶች ከግለሰብ መብቶች ጋር በእኩል እውቅና አግኝተው ካልተከበሩና ተግባር ላይ ካልዋሉ ዲሞክራሲው የተሟላ አያደርገውም ብቻ ሳይሆን የዲሞክራሲ መሰረት የሆነው ከዲሞክራሲያዊና ልማታዊ ዕድገት ጋርም በከፍተኛ ደረጃ እየጐለበተ የሚሄደው ሰላማችን አይረጋገጥም ነው። ስለዚህ በአገራችን ዲሞክራሲ የህልውና ጥያቄ ነው ስንል ሁሉም መብቶች ተግባራዊ የሚሆንበት ሁኔታ መኖር አለበት ነው። የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት የሚያስደነግጣቸውና መቀበል የሚያቅታቸው ወገኖች ዲሞክራሲን እንቀበላለን ካሉ በአገራችን ዋናው ቁልፍ ጥያቄ የሚሆነው ብዙህነታችንን የምናስተናግድበት መንገድ ያለምንም ማወላወል መቀበል ነው። ብዙህነታችንን በሚያረካ መንገድ ሳናስተናግድ ሰላም ማስፈንን እንደማይቻል ከሌላ ሳይሆን ከራሳችን ተሞክሮ መማር ስለምንችል ነው።

በአሁኑ ወቅት ሃገራችን ሁለት ዋነኛ ዓላማዎች ይዛ እየተንቀሳቀሰች ትገኛለች። በአንድ ወገን የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በሌላው ደግሞ ልማትን ማቀላጠፍና ከድህነት በፍጥነት መውጣት ብቻ ሳይሆን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሃገራት ተርታ ለመሰለፍ ነው። እንደሚታወቀው ዲሞክራሲና ልማት አብሮ ማስኬድ ይቻላል ወይስ የትኛው መቅደም አለበት በሚለው በዓለም ሊቃውንት ይህ የሚባል ስምምነት የለም። ኢትዮጵያ ግን ይህ

ይቅደም ይህ ይከተል የሚል ምርጫ ለማድረግ ዕድሉም የተሰጣት አገር አይደለችም። ዲሞክራሲያችን የሰላምም የልማትም መሰረት ነው። ልማት ተመልሶ ዲሞክራሲውንና ሰላማችንን በፅኑ መሰረት ተገንብተው ይበልጥ እያደጉ እንዲሄዱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ስለሆነም ይህ ሂደታችን በደንብ አይተን ለእያንዳንዱ የምንወስዳቸው እርምጃዎች ይሁን የምናራምዳቸው ፖሊሲዎች አንድምታቸውና ውጤታቸውን በትክክል እያየን መጓዝ ይጠይቃል። መቃወም ማለት ትርጉሙ በምትስማማው መስማማት፣ በምትቃወመው ደግሞ በምክንያታዊ መነሻ ላይ የሚደረግ መቃወም ማለት መሆኑ መታወቅ አለበት። ለዚህ ነው ለሥርዓቱ ግንባታ የቆመ፣ አገርንና የወቅቱን መንግሥት መለየት የሚችል፣ በአገር ልማትም የራሱን አስተዋፅኦ ለማድረግ የተዘጋጀና በተግባርም የሚንቀሳቀስ Loyal opposition ለዲሞክራሲ ግንባታ መተኪያ የሌለው ሚና አለው የሚባለው።

ከዚህ በላይ በሰፋት የሊበራል ዲሞክራሲ ይዘት፣ ከልማታዊ ዲሞክራሲ ጋር በዲሞክራሲውም በልማት መንገዱም ያለው አንድነትና ልዩነት በዝርዝር ለማየት ችለናል። ከዚህ ማሳያ (perspective) ተነስተን አቶ ገብሩ ሁሉንም ያነሷቸው ሳይሆን አንዳንድ ውይይት ቢደረግባቸው ይጠቅማሉ ያልኳቸውን ለማቅረብ እሞክራለሁ።

## 3. በዲሞክራሲና በዲሞክራሲ ትግል ያለው የአመለካከት ዝንፈት፣

ከፍ ብሎ እንደተገለፀው መጽሐፉ ሲጻፍ የነበሩና አሁን ያሉትን ሁኔታዎች ለመገምገም የሚያስችለውን የንድፈ ሃሳብ መነሻ (perspective) አላስቀመጠም። ሆኖም የአቶ ገብሩ ድርጅት የሚያራምደውና እሳቸውም በየስብሰባው አራምደዋለሁ የሚሉት የሊበራል ዲሞክራሲ እንደሆነ ተገልጿል። በዚህ ጽሑፍ ስለ ህውሓት ዲሞክራሲያዊ አሰራር በትጥቅ ትግል ወቅት፣ ዲሞክራሲ ለማስፈን የተደረገው ትግል፣ የዲሞክራሲ ዕንቅፋት የሆኑትን ያለፉት ሥርዓቶች አመለካከትና ተግባር በመታገል የነበረው ሂደት እሳቸው እከተለዋለሁኝ ከሚሉት የሊብራል ዲሞክራሲ መስመሮችም የማይመሳሰሉና በመስረቱ ከሞላ ጐደል በስሜት ላይ የተመሰረቱ ይመስላሉ። ዲሞክራሲ በትጥቅ ትግል ውስጥ ባለ ድርጅት ምን መምሰል አለበት? በትጥቅ ትግል ውስጥ ከዋነኛዎቹ ዓምዶች (pillars) አንዱ የሆነው በድርጅት ሕግ ብቻና ብቻ መሠረት እንቅስቃሴ ማድረግ ትርጉሙ ምንድነው? እንዴትስ ይገለፃል? በሰላማዊ ጊዜም የፓርቲዎች ዲሞክራሲና በፓርቲ ውሳኔዎች መገዛት መሃል ያለው አንድነትና ቅራኔ እንዴት ይገለጻል? በትግል ወቅት ዲሞክራሲ በድርጅቱ ብቻ ሳይሆን

ከሕብረተሰቡ ጋር ለማስተዋወቅና ብሎም ደረጃ በደረጃ እንዲጠቀምበት ለማድረግ እንዴት ይፈፀማል ወዘተ… የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በንድፈ ሃሳብ ለመመለስ ሳይሞክሩ ነው ወደ ግምገማ የዘለሉት። ስለሆነም ይህን ትልቅ ግድፈት ለማረም ከላይ የተዘረዘረውን ንድፈ ሃሳብ በመጠቀም ለማየት እሞክራለሁ።

## 3.1"በኢዴጎ እና በተሐህት መካከል የተካሄደው ጦርነት የግድ መካሄድ አልነበረበትም"?

አቶ ገብሩ በመጽሐፋቸው በገጽ 71 ላይ "እንደ እኔ ዕይታ በኢድኅና በተሓህት መካከል የተካሄደው ጦርነት የግድ መካሄድ አልነበረበትም።… የርዕዮተ ዓለም የፖለቲካ ልዩነቶች ቢኖሩም፣ እነዚህን ለጊዜው አቆይቶ ጭራሽ አላላውስ ባለው ግዙፍ አምባገነን ወይም ፋሺስት ሥርዓት ላይ ማነጣጠር ተገቢ ነበር።" ይህ አባባል በመሰረቱ ለ16 ዓመት የታገልኩበትን ፕሮግራም ትርጉም አልነበረውም፣ ፋይዳ የለውም ለማለት አሁን ያመጡት አባዜ መሆኑ ግልፅ ነው። ለማንኛውም መጀመሪያ ከተሓህት ፕሮግራም ብንነሳ ፕሮግራሙ የኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ለበርካታ ዓመታት የታገሉለትን የመሬት ለአራሹ ጥያቄና የመሬት ጥያቄውም ካለ የአካባቢውም (local) ቢሆን የሕዝብ ሥልጣን ጥያቄ እንደማይፈታ በመገንዘብ ይህን የህዝብ ጥያቄ ለመመለስ የሞከረ ፕሮግራም ነው። በግልጽ ፀረ-ፊውዳሊዝም እንደሆነም በፕሮግራሙ በማያሻማ መንገድ ተቀምጧል። ከዚህም በመነሳት ህወሓት ከጥዋቱ የህዝብ አስተዳደሮች በምርጫ እንዲቋቋሙ የሚተዳደሩበት ሕግ እንዲያፀድቁና በሕጉ መሰረት መሬት እንዲከፋፈሉ በማድረግ የፊውዳሎችን የፖለቲካና የኢኮኖሚ መሠረት እንዲፈርስ አድርጓል።

በሌላ በኩል ኢድህ ያለፈውን ሥርዓት መልሶ ወደ ሥልጣን እንዲመለስ፣ ደርግ ያወጀውን የመሬት አዋጅ ተግባራዊ እንዳይሆን የአካባቢውን ሽፍቶችና ሥራ አጥ ወጣቶች አሰባስቦ የዘመተበት ሁኔታ ነው የነበረው። ሌላ ቀርቶ አቶ ገብሩ ራሳቸው ከኢድህ መሪዎች አንዱን ለምን በትግራይ ጀመራችሁ ብለው ሲጠይቋቸው ምን እንደመለሱላቸው ማየት ይቻላል። "ደርግን በሌሎች አካባቢዎች መግጠም ይቻል ነበር፣ ሆኖም በአመራር አባላት አስቀድመን ትግራይን ካልተቆጣጠርን ለወደፊት ችግር ስለሚገጥመን ትግራይን ተቆጣጥረን ወደፊት መገስገስ እንጂ ትግራይን ከበስተጀርባ መተው የለብንም የሚል ሐሳብ

የበላይነት አገኘ" የሚል ነው።[1] ይህ ውሳኔያቸው ስህተት ነበር የሚል አመለካከት የለኝም። ምክንያቱም ሁለቱ አስተሳሰቦችና የድርጅት ፕሮግራሞች አብረው በጉርብትናም ቢሆን ሊሄዱ የማይችሉ ስለነበሩ።

አቶ ገብሩ ህወሓት/ተሓህት በወቅቱ አንገብጋቢ የነበረውን የህዝብ ጥያቄ ሳይፈታና የህዝብ አስተዳደር ሳይመሰረት እንዴት የህዝብ አመኔታ አግኝቶ እንደሚቀጥል (survive እንደሚያደርግ) በደንብ ግልፅ አላደረጉም። በፕሮግራሙ የተቀመጠውን ዓላማ በይደር አስቀምጦ ህዝቡ በመሬትና በፍትህ እጦት እየተሰቃየ አምባገነኑን ደርግ ከጣልን በኋላ ጥያቄዎቻችሁን እንመልሳለን በማለት የትግራይ ህዝብን ማሰለፍ ይቻል ነበር ወይ? በእርግጠኝነት ያኔ ጉሮሮውን አንቆ የያዘውን የመሬት ጥያቄ ቢያንስ አውገርግሮም ቢሆን የሚፈታለትን ሃይል እንደሚመርጥ ማስቀመጥ የሚቻል ይመስለኛል። ይህ የመሆን እድል ሰፊ እንደሚሆን ሌላ ምሳሌ ማቅረብ ይቻላል።

በቻይና የኮሚንታንግ ፓርቲ (China's National People's Party) በ1912 በSun Yat-Sun መሪነት ሲመሰረት የተነሳበት ዓላማ የፊውዳል ሥርዓቱን በመገርሰስ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩትን የቻይና ገበሬዎች ከጭሰኝነት ነፃ በማውጣት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመስረት ነበር። በነበረው የግራ ዘመም አስተሳሰብም በ1921 ዓ.ም. ከተመሰረተው የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ አብሮ ለመስራት በ1923 ዓ.ም.ግንባር ፈጠረ። ሱን ያት ሴን 1925 ዓ.ም. ሲሞት ሻንጋ ሼክ (Chiang Kai-shek) በእግሩ ተተካ። ሆኖም ሻንጋ ሼክ በአስተሳሰቡ ከቀኝ ክንፉ ወገን በመሆኑና በአመለካከትና በትግሉ አካሄድ በተፈጠረው ልዩነት በ1927 ኮሚኒስቶችን ከግንባሩ አባረረ። የኮሚኒስት ፓርቲ አባላት ለመጨፍጨፍና ለማሰርም ተንቀሳቀሰ።

በ1927-1949 በተካሄደው የእርስ በእርስ ጦርነት ኮሚኒስቶቹ የአርሶ አደሩን ድጋፍ ያገኙበት አንዱ ስራቸው የመሬት ከበርቴዎችን መሬት በማከፋፈል ድሆች አርሶ አደሮችን የመሬት ባለቤት እንዲሆኑ ስላደረጓቸው ነው። በተጻራሪው ኮሚንታንግ ያደረገው ነገር ቢኖር ከwarlords እና የመሬት ከበርቴዎች ግንባር በመፍጠር የኮሚኒስቶችንና የአርሶ አደሮቹን አመፅ ለመደምሰስ ነበር። በመጨረሻም የህዝቡን ድጋፍ በማጣቱ ነው። በ1949 ዓ.ም. የሻንጋ ሼክ መንግሥት ሸሽቶ ታይዋን የገባው።

---

[1]አቶ ገብሩ አስራት፣ ሉዓላዊነትና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ 2006 ዓ.ም.፣ ገፅ 72

ሻንጋ ሼክ ታይዋን ከገባ በኋላ ለሽንፈት የዳረጉን ስህተቶች ምን ነበሩ ብለው ሲገመግሙ አንዱና ትልቁ አርሶ አደሩ የመሬት ተጠቃሚ ሳያደርጉት በመቅረታቸው በሁለት መንገድ እንደተጐዱ፣ አንደኛው የገጠሩ ሕብረተሰብ ድጋፍ ማጣታቸው፣ ሁለተኛው ደግሞ የገጠሩን ኢኮኖሚ ቀስፎ የያዘውን ጭሰኝነት ባለማጥፋታቸው ጦርነቱን የሚያካሄዱበት የኢኮኖሚ ድጋፍ ማጣታቸው ነበር፡፡ በመሆኑም በታይዋን መጀመሪያ የወሰዱት እርምጃ መሬት ማከፋፈል፣ አስፈላጊውን ግብዓት በማቅረብም የግብርናውን ኢኮኖሚ ማሳደግ ነበር፡፡ እነዚህ መሰል ተራማጅ እርምጃዎች የታይዋንን ቀልጣፋ እድገት መሰረት ሆነው እነሆ ታይዋን አሁን በጣም ከበለፀጉት አገሮች ተርታ ተሰልፋለች፡፡

ስለሆነም አቶ ገብሩ ተሓህት ከኢድህ በመሞዳሞድ የህዝቡን ድጋፍ አግኝቶ ዋናው የደርግ መቺ ሃይል ይሆን ነበር ብለው ቢያስቡ አሁን የያዙት የፖለቲካ አባዜ አይናቸውን ሸፍኖአቸው ካልሆነ በቀር ከዚህ ግባ የሚባል መሠረት የለውም፡፡ ለመሆኑማ የሊብራል ዲሞክራሲ አያት ሊበራሊዚም የንጉሱንና የመሳፍንቱን ሥልጣን በመገደብ ነው የጀመረው በኋላም ፖለቲካዊና ኢኮኖሚ መሰረታቸው ነው በሂደት ያሳጣቸው፡፡ እንግዲህ የአቶ ገብሩ ፖለቲካ መነሻው በእርግጠኝነት ምን እንደሆነ ለማወቅ አስቸጋሪ የሚሆነው እዚህ ላይ ነው፡፡

ተሓህት/ህወሓት በትግራይ ገጠር ብቻ ሳይሆን በሌሎች ይንቀሳቀስባቸው የነበሩ ጉረቤት ክልሎችም የአስተዳደር ሕግ (ስሪት) እንዲፀድቅ፣ የህዝብ መስተዳደር እንዲመሰረት፣ መሬት ለህዝብ እንዲከፋፈል በማድረግ የፊውዳል ሥርዓቱን የፖለቲካና የኢኮኖሚ መሠረት በመናድ ከፍተኛ የህዝብ ድጋፍ አግኝቷል፡፡ ከመሬት ክፍፍሉ በኋላም ከድርጅቱ ዓላማም ከህዝቡ ፍላጐትም በመነጨ ለህዝብ ማህበራዊ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት እንዲስፋፉ ሆነዋል፡፡ ህዝቡ ደርግ ከወደቀ በኋላ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና ኢኮኖሚ ልማት መሠረት የሚሆን ሰላም እናገኛለን ብቻ ሳይሆን በትግሉ ጊዜም በትግላችን ያገኘነውን የመሬትና የማህበራዊ አገልግሎት ጥቅሞች አናስነካም በማለት ራሱን በማህበራት አደራጅቶ፣ መስተዳደሩን አጠናክሮ (ቆይቶ ባይቶ ማለት የህዝብ ሸንጐ መስርቶ)፣ ታጥቆ ሚሊሽያ ሆኖ በሁሉም መንገድ ተሳትፎ ታግሏል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ በ10ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ወደ ትግሉ ጉርፈዋል፡፡ እናቶች “ጥይት በግንባርህ እንጂ በጀርባህ እንዳይመታህ” ብለው ልጆቻቸው መርቀው ለመስዋዕትነት ልከዋል፡፡ ይህ

ሁሉ እውን የሆነው ተሓህት ገና በእንጭጩ ሳያወላውልና ሳያመነታ ፊውዳሎችን በመታገሉና ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መሠረታቸውን በማንኮታኮቱ ነው፡፡ በድምር በወቅቱ የነበሩ የህዝቡ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ማለትም የዲሞክራሲ፣ የብሄር ብሄረሰቦች መብትና የመሬት ላራሹን የመሳሰሉትን በወቅቱ ከተቻለ ለመመለስ ካልሆነም መልስ እንዲያገኙ የተመቻቸ ሁኔታ እንዲፈጠር በመታገሉ ነው፡፡ ሐቁ ይህ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የትግራይ ሕዝብ የተከበረ የተጋድሎ ታሪክ ሆኖ ይኖራል፡፡

አቶ ገብሩ የተሰውት የዩኒቨርስቲና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች፣ ገበሬዎችና ከተለየዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የመጡ ታጋዮች በገፅ71 ሲያነሱ ለምን እንዳነሱት ግልፅ አላደረጉም፡፡ እንደአባባላቸው ከሆነ ያኔ የተሰውት ጓዶቻችን ህይወታቸው ያለፈው በተሳሳተ የትግል ስልትና አካሄድ ነው ወደ ማለት እየወሰዳቸው ይሆን? አቶ ገብሩ እኒህ ታጋዮች ህይወታቸውን የሰውት ያን ኋላቀርና አድሃሪ ስርዓት ካልተወገደ፣ ገበሬው ከስርዓቱ ቀንበር ካልተላቀቀና የመሬት ባለቤትነት ይሁን፣ እንደ ሰው የመቆጠር መብቱ ካልተረጋገጠ በኢትዮጵያ ሰላም፣ ዲሞክራሲና ልማት ሊኖሩም ሊጐለብቱም አይችሉም ብለው ከልብ ስላመኑበት ነው ለሰው ልጅ ከህይወት በላይ ምን ሃብትና ንብረት አለውና፡፡ አሁን አቶ ገብሩ ካምፕ ስለቀየሩ እዛ ሁነው ይህን እውነታ ለማስታወስና ለማየት ተስኗቸዋል፡፡ ስለዚህም ነው ይህን የተከበረ የህዝብ ትግል ተገቢው የታሪክ ስፍራ እንዳይኖረው ላይ ታች የሚሉት፡፡ በአጠቃላይ አቶ ገብሩ እጅግ ተሳስተዋል፡፡ በድጋሜ እነዚያ ጓዶች የተሰውት የህዝቦች ዲሞክራሲያዊ መብት ለመረጋገጥ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅማቸው እንዲከበር መንገዱን ለመጥረግ ነበር፡፡ ለዚህም መስዋዕትነታቸው ክቡር ሆኖ ለዘለአለም ሲታወሱ ይኖራሉ፡፡

አቶ ገብሩ የኢድህ በሽግግር መንግሥት ተሳትፎ ሲያነሱ መጀመሪያ ከህወሓት ጋር ሂሳብ ማወራረድ ነበረበት ማለታቸው ከሆነ እርግጠኛ ነኝ ፖለቲካ አይሆንም፡፡ ድርጅቶች በየጊዜው ከሁኔታው ጋር ፕሮግራማቸውን እያሻሻሉና እየለወጡ እንደመጡ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሂደት ያሳየን ይመስለኛል፡፡ የ1967ቱና 1968ቱ ኢህአፓና 1980ዎቹ ኢህአፓ ምንኛ እንደሚለያዩ በፕሮግራማቸው ማየት ይቻላል፡፡ አይንና አመድ የነበሩት መኢሶንና ኢህአፓ ኢድዩንና EPDAን ጨምረው Coalition of Ethiopia Democratic Forces (COEDF) በ1980ዎቹ መጀመሪያ የመሰረቱበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ደርግ በመጨረሻ ጊዜ ባደረገው የሸንጐ ስብሰባ በአንድ በኩል "ለአንድነት ኃይሎች" የሰላም ጥሪ ሲያውጅ በሌላ

በኩል ደግሞ ሰፊ የክተት አዋጅ አወጀ።[1] COEDF የሸንጐውን አዋጅ ደግፎ መግለጫ ወዲያውኑ አወጣ።[2] በወቅቱ ኢህአዴግ COEDF የደርግን የጦርነት አዋጅ መደገፉ ስህተት መሆኑን መግለጫ አውጥቶ ማውገዙ ይታወሳል። ግንቦት 1983 ዓ.ም. የለንደን ኮንፍረንስ ውጤቶችን COEDF አውግዞ በሽግግር ኮንፍረንሱ ግን መሳተፍ እንደሚፈልግ ገለፀ። ከኢህአዴግ የተሰጠው "ቅድመ ሁኔታ" ቢኖር COEDF ጦርነቱን እንዲያወግዝና ለሰላማዊ ትግል ያለውን ዝግጁነት (commitment) በግልፅ እንዲያውጅ ነበር። COEDF ይህን ሰላምን የመቀበልና ለሰላማዊ ትግል የመቆምን ጥሪ መቀበል አልፈለገም። በዚህም ምክንያት እንደ ጥምረት ከመሳተፍ ተከለከለ።

አቶ ገብሩ የነበረውን ሂደት እያወቁ ለምንድነው በገጽ 181 "የሽግግር ቻርተሩ በዛው አስቀራቸው" የሚሉት። ፕሮግራማቸው ይታወቃል በሰላም ገብተው መንቀሳቀስ እንደሚችሉ ተነግሯቸዋል። ከላይ እንደገለጽኩት የተጠየቁት ለሰላማዊ ትግል ያላቸው ዝግጁነትና ከዚህ ውጭ ያለውን የትግል አማራጭ ኮንነውና በግልጽ ለህዝብ አሳውቀው ወደ ተፈጠረው የፖለቲካ ሜዳ እንዲቀላቀሉ ነው። አቶ ገብሩ የወቅቱ ጓደኞችዎን ለማስደሰትና ድጋፍ ለማግኘት ከሆነ እንደ የፖለቲካ ብልጥነት (poltical expediency) ልወስደው እችላለሁ።

በዚህ መሃል ግን ኢድዮ የጥምረቱን አቋም ተቃውሞ በተለይም ለሰላማዊ ትግሉ ያሳየው የእግር መጐተትና ለትጥቅ ትግል መቀጠል ያሳየው አፍቅሮ አውግዞ በሽግግር ኮንፈረንሱ እንዲሳተፍ ጠይቆ፣ ሰላማዊ ትግልን እስከተቀበለ ድረስ በኮንፈረንሱ እንዲሳተፍ መደረጉ ስህተቱ ምን እንደሆነ አቶ ገብሩ ለራሳቸውም ግልፅ የሆነላቸው አይመስልም። የ1980ዎቹ ኢድዮ ፕሮግራሙ ይሁን ከፕሮግራሙ የመነጩ አቋሞች በሽግግሩ ኮንፈረንስ መሳተፍ የሚያስከለክሉት አልነበረም። ከ1960ዎቹ የተለየ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረት እንደተፈጠረ መገንዘብ ያስፈልጋል። ኢድህም በ1980ዎቹ ባለው ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ያንቀሳቅሰኛል፣ የህዝብ ድጋፍ ያስገኝልኛል ብሎ ያሰበውን ፕሮግራም ይዞ ነው በአዲሱ መድረክ የተሳተፈው። ስለሆነም "የሂሳብ ማወራረድ" ፖለቲካ ውስጥ ከገባን የእርስዎ የዘመኑ ጓዶችንም የኋላ ታሪክ ወደ መቆፈር ስለሚያስኬድ የሚያዋጣ አይደለም። በመሰረቱ ግን ድርጅት የሚመዘነው በወቅቱ በያዘው የፖለቲካ አቋም ስለሆነ

[1] የብሔራዊ ሸንጐ ውሳኔዎች፣ ሚያዝያ 1983 ዓ.ም.
[2] የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ኃይሎች ጥምረት፣ የሥራ አስፈጻሚ መግለጫ፣ ሚያዝያ 1983 ዓ.ም።

በዚሁ ብቻ ቢወሰን መልካም ነው። በድሮው ኢዲህ (የ1968ቱና 69ኙ ኢድህ) ላይ የያዙት አቋም ግን በመሰረቱ የተፋለሰና ከባድ ስህተት እንዲሁም የተከፈለውን መስዋእትነት የሚያጣጥል መሆኑን ለማስገንዘብ እወዳለሁ።

## 3.2 ዲሞክራሲያዊ ማዕከልነት (Democratic Centralism) በተመለከተ፣

ዲሞክራሲያዊ ማዕከልነት ድርጅቶችና ፓርቲዎች የቆሙለት ዓላማ በአግባቡ ተግባር ላይ እንዲውል የሚጠቀሙበት የሃሳብና ተግባር አፈጻጸም አካሄድ ነው። ብዙ ጊዜ ዲሞክራሲያዊ ማዕከልነት በሌኒን ጽሑፎችና አንደበት ተደጋግሞ ስለተጻፈና ስለተነገረ ከግራ ክንፍ አመለካከት ጋር ተያይዞ ይነሳል። ሌኒን ዲሞክራቲክ ማዕከልነትን “freedom of discussion, unity of action” ብሎ ገልጾታል። ይህ ማለት በአንድ ፖለቲካዊ ጉዳይ ላይ በፓርቲው መዋቅር ከታች እስከ ላይ ሰፊ ውይይት ይካሄዳል። ውይይቱ አልቆ በአብዛኛው ተሳታፊ ውሳኔ ላይ ከተደረሰና ከፀደቀ በኋላ ግን ሁሉም እንደ አንድ ሰው ወደ ስራ ይገባል ነው። የተወሰነውን ውሳኔ የመፈፀምና የማስፈፀም ግዴታ አለበት ማለት ነው። በፓርቲያቸውም ይህን አሰራር ተግባራዊ ለማድረግ ተግተው ሰርተዋል። ሆኖም ይህ አሰራር ለኮሚኒስት ፓርቲዎች ብቻ የተተወ አሰራር አይደለም። በምዕራብ ፓርቲዎችም ፕሮግራማቸውንና ማኒፌስቶቻቸውን በፓርቲያቸው ጉባኤ ወይም ኮንፈረንስ ካፀደቁና ለሕዝብ አስተዋውቀው ተመርጠው የመንግሥት ሥልጣን ከያዙ በኋላ እነዚህ በፕሮግራማቸውና በማኒፌስቶቻቸው ላይ የተዘረዘሩት ተግባራት እንደየሁኔታው ወደ ፓርላማ እየቀረቡ በአዋጅ ወይም ወደሚኒስትሮች ምክር ቤት በመውሰድ እንደደንብ ሆነው በመንግሥቱ መዋቅር አማካኝነት ተግባራዊ ያደርጓቸዋል።

የምዕራብ ፓርቲዎች ፕሮግራማቸውንና ማኒፌስቶቻቸውን ሲያፀድቁ በየመሰረታዊ የፓርቲ ድርጅቶች ሰፊ ውይይት ተደርጕበት ከዛም በጉባዔዎቻቸውና ኮንፍረንሶቻቸው የተለያዩ ሃሳቦች ቀርበው ከተፋጩ በኋላ በድምፅ ብልጫ ውሳኔ ላይ ይደርሳሉ። ውሳኔዎቹ የፓርቲዎቹ የፕሮግራምና የማኒፌስቶዎች ይዘት ብቻ ሳይሆን የተወሰነ የአቀራረብ መስተካከል ተደርጕባቸው የምርጫ መወዳደሪያቸው ይሆናሉ። ከተመረጡም በኋላ ቅድም እንደተገለፀው ወደ ተግባራዊነታቸው ይለውጡዋቸዋል።

እንግዲህ ተግባራዊ ከመሆናቸው በፊት ዋናዎቹ ሃሳቦች በፓርላማ መፅደቅ ስላለባቸው ወደ ፓርላማ ይቀርባሉ። ሁሉም የፓርላማ አባል እንደፈቀደው ይመርጣል ማለት አይደለም። በፓርላማው party whip የሚባሉ የፓርላማ አባላት ፓርቲያቸው በሚፈልገው መንገድ እንዲመርጡ የሚያደርጉና የሚያስገድዱ ኃላፊዎች ከሞላ ጐደል በሁሉም የምዕራብ አገሮች አሉ። ይህ ማለት ድምፅ ለመስጠት እንጂ ሁሉም እንደሚያውቀው በፓርላማው ፀድቆ አዋጅ ከሆነ በኂላ እያንዳንዱ ዜጋ አዋጁን የማክበር ግዴታ አለበት። ይህ ለማንም ዜጋ ግልፅ ስለሆነ በድምፅ አሰጣጥ ላይ ያሉ አሰራሮች (practices) ለማሳየት ትኩረት ሰጥቻለሁ። ምሳሌ መጥቀስ ከተፈለገ የፓርላሜንታዊ ዲሞክራሲ መመንጫ በሆነው የዩናይትድ ኪንግደም ፓርላማ Chief Whip የሚባል ሹመት አለ። በካቢኔም Parliament Secretary to the Treasury ተብሎ ይቀመጣል። Chief Whip እና ረዳቶቹ የፓርላማ አባላት እንዴት ድምፅ መስጠት እንዳለባቸው ሦስት ዓይነት መመሪያዎች ይሰጣሉ። አንዱ single-line whip ይባላል። ይህ መመሪያ የፓርላማ አባላት ከፈለጉ በፓርላማው ይገኛሉ። ከፈለጉ ይመርጣሉ። ዋናው ነጥብ መቼና በስንት ሰዓት ድምፅ እንደሚሰጥ ያሳውቃሉ። ሁለተኛው two-line whip ይባላል። ፓርላማ አባላት እንዲገኙና እንዲመርጡ የሚተላለፍ መመሪያ ነው። በተወሰነ ደረጃ እንዲገኙም እንዲመርጡም የሚያስገድድ ነው። ሦስተኛውና ዋናው ግን three-line whip የሚሉት ነው። ይህ እንዲገኙም ፓርቲው በሚፈልገው መንገድ እንዲመርጡ ያስገድዳል። ይህን አለመከተል ከፓርላሜንታዊ ፖለቲካዊ ቡድን እንዲሁም ከፓርቲው አባልነት ጨርሶ የመባረርን ቅጣት ያስከትላል። ይህ ነው መብት ብቻ ሳይሆን ግዴታም አለ የሚያስብለው።

ይህ አሰራር በአሜሪካ ሳይቀር ይሰራበታል። በኮንግረስ ሁለቱም ፓርቲዎች የየራሳቸው whips አላቸው። እነዚህ whips ዋና ስራቸው በኮንግረስ የፓርቲ ዲሲፕሊን እንዲከበር ነው። የአሜሪካኖች አሰራር የኮንግረስ አባላት ከአካባቢያዊ የምርጫ ክልሎቻቸው በጣም የተቀራረበ አሰራር ስላላቸው አንዳንድ ጊዜም አባላቱ በየአካባቢው ያለውን አመለካከት መሰረት አድርገው ድምፅ ስለሚሰጡ የማባረሩ ቅጣት ተግባራዊ አይሆንም። ቅጣቱ ሌላ መልክ ይዟል። የHouse or Senate Commitees መሪ ከነበረ እንዲወርድ ይደረጋል፣ መሾም ከነበረበትም ይዘለላል። ለምርጫ የሚሆን ገንዘብ ሲደለደልም እንዲሁ ቅጣቱን ያገኛል። በተለይ በአሜሪካ ኮንግረስ የኮሚቴ ሊቀመንበር መሆን ከፍተኛ ሥልጣንና

ለመረጠው ህዝብ ብዙ ለመስራት ስለሚያስችለውና በተደጋጋሚ የመመረጡ ዕድልም እርግጠኝነት ስለሚያሰፋለት ያን ማጣት ማለት ትልቅ ቅጣት እንደሆነ ይታወቃል።

ሌላም ከእነዚህ ሁለቱ በጣም ጠበቅ ያለ የፓርላማ አባላት ዲሲፕሊን የሚጠየቅበት አውስትራሊያን ማየት ይቻላል። የአውስትራሊያን whips ሁሉም የፓርላማ አባላት በፓርቲያቸው ፍላጐትና መንገድ መሰረት ድምፅ እንዲሰጡ ያስገድዳሉ። እንደሚታወቀው የተለያዩ ፓርቲዎች ያለበት አገር ስለሆነ በፓርቲዎቹ የተወሰነ ልዩነት መኖሩ አልቀረም። ስለሆነም በሁለቱ ትላልቅና የመንግሥት ሥልጣንም በሚፈራረቁት ፓርቲዎች ውስጥ ያለውን አሰራር ማየቱ በቂ ይሆናል። በLiberal party በፓርቲው ፍላጐት መሰረት ድምፅ አለመስጠት የተለያዩ ቅጣቶች አሉበት። አንዱ የexecutive ሥልጣን የመያዙ ዕድል ዝግ ሲሆን በተጨማሪም በpre-election ጊዜ ሌላ የፓርቲው ተአማኒ ሰው እንዲወዳደረው (challenge) እንዲያደርገው ይደረጋል። በምርጫው ሂደትም የፓርቲው ድጋፍ ያጣል። በLabour Party ግን ከፓርቲው መመሪያ ውጭ ድምፅ መስጠት ቅጣቱ ከፓርቲው መባረር ነው።

የብዙ የአውሮፓ አገሮች የአሰራር ምሳሌዎች ማቅረብ ይቻላል። የተለያዩ የፓርላማ አባላት ዲስፒሊን ማስጠበቂያ አሰራር አይተናል። እንደሌኒን ዲሞክራሲያዊ ማዕከልነት ባይሉትም ይዘቱ በምንም የሚለይ አይደለም። አንድ ሓቅ እንደየሃገሩ ሁኔታ የተወሰነ ልዩነት መኖሩ ነው። ዋናው ቁም ነገሩ ግን የፓርቲዎች አሰራር ሥርዓተ-አልበኝነት (anarchism) የሚጋብዝ ሳይሆን መብትን ሲያስከብር ግዴታና የተግባር አንድነት እንዳለና በአግባቡ እንደሚጠበቅ መገንዘብ ያስፈልጋል። ለነገሩማ whip የአደን ውሾች እንዳይበታተኑና አደኑ ሳይሳካ እንዳይቀር እንዲሰባሰቡና ሃይል እንዲሆኑ ለማድረግ አዳኞች ከሚጠቀሙበት ቃል “whipping in” የመጣ መሆኑ መገንዘቡ ጠቃሚ ይሆናል።

ይህን ካየን በኂላ አቶ ገብሩ የህወሓትን ዲሞክራቲክ ማዕከልነት በነበረው ሁኔታ አስቀምጠው ለምን ማየት እንዳቃታቸው ነው የሚገርመኝ። በመጀመሪያ መግባባት ያለብን ሁላችንም የመጣነው የዲሞክራሲ ሽታ ሽቶት ከማያቀው ሕብረተሰብ ነው። ሁለተኛ በጦርነት ውስጥ ያለ ድርጅት መሆኑ ደግሞ ሌላው ተጨባጭ ሁኔታ ነው። በድርጅቱ የጦርነት ሁኔታዎች ሳያግዱት ሰፊ ውይይትና ክርክር እየተደረገ ወደ ጉባዔ ተኪዶ ነበር መሠረታዊ ውሳኔዎች ይፀድቁ የነበሩት። ከዛም የፀደቁትን ውሳኔዎች በጠንካራ ዲሲፕሊን ተግባራዊ ይደረጉ ነበር። ሌላ ቀርቶ አመራሮቹንም በየጉባኤው ሲያወርድና ሲመርጥ የነበረ

ድርጅት ነው። በትጥቅ ትግሉ ወቅት የስትራቴጂና የፖሊሲ ልዩነት ያነሱ አመራሮችም ሳይቀር መድረክ ተፈጥሮላቸው ሐሳባቸውን አቅርበው በሰፊው ከተከራከሩ በኋላ ሲሸነፉና ድርጅቱን ለቀው መሄድን ሲመርጡ በሰላም የሚሰናበቱበት ድርጅት እንደነበር ይታወቃል። ይህ አውነታ ነው። ግን ለምንድነው ይህ አሰራር አቶ ገብሩ የነቀፉት? የአፈጻጸም ዲሲፕሊን ባይኖረው ያን ትልቅ መንግሥት መጣል ይቻል ነበር ይላሉ። ህወሓት ፖለቲካዊ ሠራዊት ስላለው ነው እንጂ ሌሎች የምዕራብ ሠራዊቶች እንዴት እንደሚሰሩ አያቁም? ውስጠ ዲሞክራሲያቸው ምን እንደሚመስል ትንሽ ጥናት ቢጤ ለማድረግ ሞክረዋል?

አቶ ገብሩ በመጽሐፍዎ ገፅ 84 ሲገልፁ "ከዲሞክራሲው ማዕከልነቱ ይጠብቅ ነበር" ይላሉ። ተዋጊ ሃይል በሆነ ኢንስቲቱሽን የመዋጋት ችሎታውን በማይቀንስ መንገድ ዲሞክራሲው ከነበረው በላይ ማስፋት ይቻላል ወይ? ይህ ጥናት ማድረግ የሚጠይቅ ይመስለኛል። የነበርንበት ሁኔታም በትልቁ ግምት ውስጥ ማስገባት ይጠይቃል። እዚህም እዛም መሰራት የነበረባቸው የቀሩ እንደነበሩ እኔም እገምታለሁ። ከዛ ግን ህወሓትን ወደ "talking shop" የሚቀይር አመለካከት ግን ፍፁም ስህተት ነው። ሌላ የምዕራባውያን ሠራዊቶች የሚሰሩበት ሁኔታ ማለት በ"command and obedience" ነው የሚሰሩት። ይህንን ያነሳሁት ህወሓት ከእነሱ ለማነፃፀር አይደለም ግን በጦርነት ውስጥ ያውም አብዛኛው ዕድሜውን በሽምቅ ወጊያ ያሳለፈ ድርጅት በጣም ጥሩ ሠርተዋል የሚያስብል አካሄድ ነው የነበረው። እንደሚታወቀው ስህተቶች ሲፈፅምም ያለምህረት እየገመገመና እያስተካከለ ነው የመጣው። ስለዚህም ነው ትልቅ ሃይል ሆኖ የደርግን መንግሥት ከአጋሮቹ ጋር በመሆን ያሽመደመደው።

ሌላው ግን የህወሓት አካሄድ ሲተቹ "ይህ አካሄድ የዜጐች ነፃነት፣ የሕግ የበላይነት፣ የሰብዓዊ መብቶችን፣ ነፃ ዳኝነትን፣ የሃሳብና የድርጅት ብዙህነትን ወዘተ… ከሚያረጋግጠው እውነተኛና አይነተኛ ዲሞክራሲ አብሮ የሚሄድ አልነበረም" ሲሉ ምን እንደሚሉ ጭራሹን የሚገባ አይደለም። እንኳን ህወሓት በትጥቅ ትግል ውስጥ የነበረ ድርጅት በሰላም ስራቸውን በሚሰሩ በምዕራብ አገሮችም ጭምር ይህ እርስዎ የሚሉት በተሟላ ተግባራዊ ማድረግ አስቸጋሪ እንደሆነ አልተረዱም። ይህን ያሉትን በተሟላ መንገድ የሚተረጉም መንግሥት እስከአሁን የለም ብሎ እኮ ነው Dahl "Polyachy" የሚላቸው ትርጉሙም የብዙሃን አገዛዝ ማለት እንደሆነ ቀደም ብዬ ገልጨዋለሁ።

ህወሓት በውስጡና በሕዝቡ ዲሞክራሲያዊ አሰራርን ለመከተልና ለመተግበር እየታገለ መጥቷል። በሌላ አቀራረብ የነበረው አሰራር ህወሓትን ወደ ትልቅ ሃይል ለውጦታል። ከህዝቡም ያለምንም ተአቅቦ (reservation) ከፍተኛ ድጋፍ አግኝቶ ለድል በቅቷል። እኔ እንደሚመስለኝ አቶ ገብሩ አሁን መፈላሰፍ የጀመሩ ይመስለኛል። “Power and order”፣ “command and obedience” አኩልነትና ነፃነትን የሚጻረር ነው፣ “use of force” የ“non-violence” ዲሞክራሲያዊ ideal ይቃረናል ወዘተ… እያሉ ወደ ሌላ ህልማዊ ዓለም እንዳይሸጋገሩ ስጋት አለኝ።

የሆኖ ሆኖ አቶ ገብሩ አሁን ወደ ሌላኛው ካምፕ ከተሸጋገሩ በኋላ ረሱት እንጂ ህወሓት በጉባኤ ባፀደቀው ህግና ደንብ የሚመራና በነበረው ሁኔታም በተቻለ መጠን ህጉንና ደንቡን ተግባራዊ አድርጓል። ማንም ሰው እዚህ ጉድለት ነበር እዛ ጉድለት ነበር ብሎ ማንሳት ይችላል። የትኛውስ ሥርዓትና መንግሥት ጉድለት የማይነሳበት። በአጠቃላይ ግን ሂደቱ አዎንታዊ ስለነበር ነው ሌሎች ሲበተኑ ህወሓት survive ማድረግ ብቻ ሳይሆን ዋንኛ መቺ ሃይል (formidable and effective force) ለመሆን የበቃውና አሁን እንዲህ እንድንነጋገር የሚያስችል ሁኔታ እንዲፈጠር የራሱን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገው። አቶ ገብሩ የዲሞክራሲ አንዱ ምሰሶ (pillar) የህግ የበላይነት መሆኑን መርሳት የለበዎትም። የሕግ የበላይነት ለሁሉም፣ የትም ይሰራል። ጀርመኖች Rechtsstaat ይሉታል። ይህን ተከትሎ Juan Linz “no state, no Richtsstaat, no democracy” ይላል።[1] በመጨረሻም ወደ ኋላ ተመልሼ ትልቁ ፈላስፋ Montesqieu ከዛሬ 250 ዓመት በላይ የሚከተለውን ብሎ ነበር። “Liberty is the right to do everything the laws permit”. ሕግ ማክበርና ሕግን ተሞርኩዞ መስራት የነፃነት መሰረትም ነው።

ሌላ መታየት ያለበት ጉዳይ ህወሓት/ኢህአዴግ ዋናዎቹ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ቀርጾ ከዛም ያለፈውን የስራ አፈጻጸሙን ግምገማ በተገቢው መንገድ አቅርቦ ነው ለምርጫ የሚቀርበው። ሲጀምር ሲወዳደር እነዚህን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እፈፅማለሁ፣ አስፈፅማለሁ ብሎ ነው። አንዳንድ ሰዎች በፓርላማ ኢህአዴግን ወክሎ ተመርጦ የሚገባውን አባል የፖሊሲና የስትራቴጂ ክርክር እንዲያነሳ ይጠብቃሉ። ይህ ከፍተኛ

[1] Juan J. Linz, “Democracy Today: An Agenda for Students of Democracy,” Scandinavian Political Studies 20, no.2, 1997:118.

ስህተት ነው። የትም አገር ቢሆን ፓርቲዎች ለሥልጣን በሚወዳደሩበት ጊዜ ዋናዎቹ ፖሊሲያቸውና ስትራቴጂያቸውን አቅርበው ነው የሚመረጡት። ስለሆነም የፓርላማ አባላት ሚና እነዛ ህዝቡ የመረጣቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ማስፈፀሚያ የሚሆኑ አዋጆችና ዕቅዶች ሲወጡ የበለጠና ውጤታማ በሆነ መንገድ የሚፈፀሙበትን ይዘት እንዲኖራቸውና ይዘው እንዲወጡ የሚደረገው ክርክር ከፍተኛ ስፍራ ይሰጠዋል። ለዚህ ነው ፓርላማው ዓመቱን ሙሉ የሚሰራቸው የሕግ ማውጣት (Legislation) ስራዎች በዓመቱ የፓርላማ መክፈቻ ወቅት በገዥው ፓርቲ አዘጋጅነት በHead of State ንግግር የሚገለፀው። ይህ ማለት አስቸኳይ የሆኑ በሂደት የሚፈጠሩ ነገሮች አያይም ማለት አይደለም። ፓርላማው በተቀመጠበት የሥራ ዓመት የሰራውን ስራ ለመመዘንና ለመገምገም የሚያስችል ግን ዕቅድ ይኖረዋል ማለት ነው። ከዛም በመቀጠል የሚፈፀሙት ዕቅዶች አስፈጻሚው ክፍል በአግባቡ መስራቱንና አለመስራቱን በተለይም ወደ ፓርላማ መድረክ ከመቅረባቸው በፊት የህዝብ አደረጃጀቶችና ግለሰቦችም ቢሆን እንዲሳተፉ መድረክ እየፈጠሩ፣ የህዝቡን አስተያየት እንደግብዓት እየተጠቀሙ ያለምህረት መገምገምና ማስተካከያ መስጠት ነው። ሁኔታዎች በአግባቡ ካልሄዱ ደግሞ ከብዙ የማስተካከያ ጥረት በኂላ በአስፈጻሚ ወይም አስፈጻሚዎች ላይ የተቃውሞ ድምፅ (vote of no confidence) ማሳለፍ ነው። ስለሆነም ፓርላማው ምን ያህል ክርክር ያደርጋል፣ ምን ላይስ ድምፅስ ይሰጣል፣ የሚለው ግልፅነት ቢኖረን ምን ሰራ፣ ምንስ አልሰራም ለመለየት የተሻለ ዕድል ይኖረናል። ይህ እንግዲህ የየአገሩ ሕገ-መንግሥት ለፓርላማው የሚሰጠው ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር እንደሚያከናውንም እንደተጠበቀ ነው።

## 4. የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትና ፌደራሊዝም፣

የብሄሮችና ብሄረሰቦች መብት የመከበር ጥያቄ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ትግል ከፍተኛ ስፍራ የነበረውና ያለው መሆኑ ይታወቃል። የኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴ የብሄሮች መብት መከበር ካነገባቸው ዋና ዋና ጥያቄዎች ጉልቶ የሚታይ ጥያቄ ነበር። ከዛም የኃይለሥላሴ መንግሥት ወድቆ የደርግ አገዛዝ ሲተካ በርካታ ብሄሮችና ብሄረሰቦች ጥያቄውን አንግበው ለመብታቸውና ለነፃነታቸው ታግለዋል። በመጨረሻም ደርግን አስወግደዋል። ይህ ጥያቄ አእላፍ ዜጐች ህይወታቸውን መስዋዕት የከፈሉለት በመሆኑ በሽግግር ቻርተሩ ከዛም በሕገ መንግሥቱ የተሟላ ዕውቅናና መፍትሄ አግኝቷል።

በሕገ መንግሥቱ የግል ነፃነት የሚባሉት በዝርዝር የተቀመጡ ሲሆን የቡድን መብቶቹም በተገቢው መንገድ ተቀምጠዋል፡፡ እነዚህ የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብትና የግሉ መብቶች ሳይነጣጠሉ ተግባራዊ መሆን እንዳለባቸው ሕገ መንግሥቱ በግልፅነት (unequivocally) ያስቀምጠዋል፡፡ ከዚህም በመነሳት መንግሥትም ህዝብም መብቶችን ለማስከበር፣ ከጊዜ ጊዜም እየተጠናከሩ፣ እየጐለበቱ እንዲሄዱ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

አቶ ገብሩ መብቱን ተቀብያለሁ ብለው ይነሱና ከዛ በመቀጠል በገፅ 479 "በኢህአዴግ ዘመን ከፍተኛ ፈተና የገጠመው ይኸው የምልአተ ህዝብ መለያ የሆነው ኢትዮጵያዊነት ክፉኛ መመታቱና በተለይ ለዚህ የኢትዮጵያዊነት እሴት ግንባታ ጠቃሚ የሆኑ መለያዎች መሸራረፋቸው..." ነው ብለዋል፡፡ እዚህ ላይ ሁለት ጉዳዮች አንስተዋል፡፡ አንዱ ኢትዮጵያዊነት ሲሆን ሁለተኛው የኢትዮጵያዊነት እሴቶች ግንባታ በተመለከተ ነው፡፡ እነዚህን አንድ በአንድ ለማየት በኢትዮጵያዊነት እንጀምር፡፡ አቶ ገብሩ የትኛው "ኢትዮጵያዊነት" ነው የተመታው፡፡ የመሳፍንቱ፣ የመኳንንቱና የደርግ አምባገነኖች "ኢትዮጵያዊነት" ወይስ የህዝቡ፣ የኢትዮጵያ ብሄሮችና ብሄረሰቦች፡፡ ከመጽሐፍዎ የማየው "ኢትዮጵያዊነት" ያየተለመደው የውሑዳንና ፅንፈኞች "ኢትዮጵያዊነት" ይመስላል፡፡ አብዛኛውን ህዝብ የማያቅፍ፣ በርካታ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እስከመኖራቸውም እንኳን ዕውቅና የማይሰጥ "ኢትዮጵያዊነት" ፀረ-አንድነት፣ ፀረ-ሰላምና ፀረ-ልማት ነው፡፡ ይህ እርስዎ የሚሳሱለት "ኢትዮጵያዊነት" ያከተመለት ይመስለኛል፡፡ በዛው በርስዎ "ኢትዮጵያዊነት" መቃብር ላይ አዲስና ዲሞክራሲያዊ ኢትዮጵያዊነት የመገንባቱ ትግል ተጧጡፎ ቀጥሏል፡፡

ሁለተኛ የጋራ እሴቶችን ስናነሳ በጐ ገፅታና አሉታዊ ገፅታ እንዳላቸው መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የእሴቶቻችን በጐ ገፅታዎች ለአንድነታችን መሰረት የሆኑ የጋራ ጠላትን በመከላከል ነፃነታችንን ጠብቀንና አስጠብቀን የኖርን ህዝቦች መሆናችን፣ በታሪክ፣ በባህልና ሃይማኖት፣ በኢኮኖሚም መዳበር ያለባቸው ትስስሮች እንደነበሩና እንዳሉ መቀመጥ ይኖበታል፡፡ በሌላ በኩል ባለፈው ሥርዓት የነበረው የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ጭቆና በበጐ የሚገለፁትን እሴቶች ሲሸረሽሩ፣ በመጨረሻም ወደ አስቸጋሪ ሁኔታ ገብተን እንደቆየን ይታወቃል፡፡ ስለዚህ አቶ ገብሩ የጋራ እሴቶቻችን ተሸርሽረዋል ሲሉ የትኞቹ እንደሆኑ በግልፅ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በጐ የጋራ እሴቶቻችንን ሲሸረሽሩ ወደ መበጣጠስ ሊያደርሱን የነበሩት በጐ ያልሆኑ እሴቶች አሁን በተፈጠረው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብት መከበር እየተወገዱ ናቸው፡፡ እነዛ በበጐ የሚታዩ የጋራ

እሴቶቻችን መሰረት አድርገን አንድ ጠንካራ የጋራ የኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ማህበረሰብ ለመፍጠር ተስማምተን በሕገ-መንግሥታችን ኮለል ብለው ተቀምጠው፣ በተግባርም ከፍተኛ ርብርብ የምናደርግበት ወቅት ብቻ ሳይሆን አመርቂ ውጤትም እያገኘንበት ነው። ታዲያ አቶ ገብሩ ፀረ-ህዝብ፣ ፀረ-እኩልነትና ፀረ-ልማት "እሴቶች" መሸርሸራቸውና መዳከማቸው ነው እያናገራቸው ያለው? ከዚሁ እንደማይዘል ነው መቀመጥ ያለበት።

የህዝቡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊነትና በጐ የሆኑ የጋራ እሴቶቻችን ከዳር እስከ ዳር አሁን ነው እየጐለበቱ እየመጡ ያሉት። የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች የራሳቸውን መብትና ነፃነት አስከብረው በአንድነት ደግሞ የአሁንዋ ኢትዮጵያችን በጠንካራ መሰረት እየገነቧት ያሉት። ኢትዮጵያችን በታሪክዋ ከራስዋ ጋር ሰላም የሆነችበት ዘመን አለ ቢባል የአሁኑ ዘመን ነው። ይህ ሥርዓት ደግሞ በዲሞክራሲውና በልማቱ ግንባታ እየጐለበተና እየተጠናከረ የሰላማችን መሰረት እያጠናከረ እንዲሄድ አሁንም ቢሆን ያላሰለሰ ትግል ይጠይቃል። በትግላችንም ውጤት እያገኘን እንደምንሄድ የሚያጠራጥር አይሆንም።

ከዛም ወረድ ሲል በፌዴራሊዝም ላይ የሚሉት ነገር የሚገርም ነው። "የኢትዮጵያ ፌደራላዊ አወቃቀር መሠረታዊ ችግር 1ኛ ዴሞክራሲን የሕግ የበላይነትን የዜጎች ነፃነትን ሳያከብር ስራ ላይ መዋሉ፣ 2ኛ. በፌዴራል ክልሎች ያለው የመወሰን ሥልጣን በእነዚህ ክልሎች ላለው ህዝብ የተሰጠ ሳይሆን ለገዢው ፓርቲ አመራር የተሰጠ በመሆኑ ነው።" ዲሞክራሲ፣ የሕግ የበላይነት፣ የዜጐች ነፃነት መከበር ያዋጅ ጉዳይ ብቻ አይደለም። በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ህዝቦች በመራራ ትግላቸው በሕግ መንግሥቱ እንዲሰፍር፣ የዲሞክራሲ ተቋሞች እንዲፈጠሩና እንዲጐለብቱ ትግል እያደረጉ ናቸው። በየትኛውም የፌዴራል ሥርዓት ሃገራት ዲሞክራሲውም የፌደራል ሥርዓቱም ጐን ለጐን ነው ለመገንባት ጥረት የሚያደርጉት። ፌዴራሊዝም ለጌጥ የሚመሰረት ሥርዓት አይደለም። Simpson እንደሚለው "Federalism emerges out of necessity, crisis-situation, or compulsion. It evolves from concrete and tangible needs or pressures". በኢትዮጵያም Simpson እንዳለው የነበረውን የብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ጭቆና ለመፍታት፣ ሕዝቦች የራሳቸውን ከባቢያዊ ጉዳይ ራሳቸው እንዲያስተዳድሩ፣ የዲሞክራሲና የልማት እጦት ችግራቸው እንዲፈታ የፌደራል ሥርዓት የገነቡት። በፌዴራል መንግሥቱ ምስረታ ይሁን አካሄድም ተገቢ ሚናቸውን በመጫወት ላይ ናቸው። ይህ ሂደት ከጊዜ ወደ

ጊዜ እየበለጠ፣ እየተሻለ፣ እየረቀቀና መሰረቱን እየሰደደ የሚገኝ እንደሆነ ለማየት የሚያስቸግር አይደለም።

ፌዴራል ሥርዓቱ "ለገዥ ፓርቲ አመራር የተሰጠ እንጂ ለህዝብ የተሰጠ አይደለም" የሚለው አባባል ያሁሉ የዘመሩለት ዲሞክራሲ ተመልሰው ትርጉም አልባ እያደረጉት ነው። አቶ ገብሩ ምን ማለት ነው የመወሰን ስልጣን ለህዝብ መስጠት ማለት። ኢህአዴግ የሚከተለው ልማታዊ ዲሞክራሲና በህዝብ ተሳትፎ ያለው አመለካከት ከላይ ተዘርዝሯል። በታችኛው መዋቅር ማለት በቀጥታ በዲሞክራሲውም በልማቱም ግንባታ የሚሳተፍበት ከዛ ከፍ እያለ ሲሄድም የዲሞክራሲ ንድፈ ሃሳብ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና (representation) የሚሰራ አካሄድ ነው። ህዝቡ በፓርቲዎች በቀረቡለት አማራጭ ወኪሎቹን እየመረጠ ነው። የተለያዩ የዲሞክራሲ ተቋማት (institutions) ይህን የዲሞክራሲ ግንባታ ውጤታማ እንዲሆን እየሰሩ ነው። ይህ ስራ በትግል ክፍተቶቹን እየሞላ፣ ጉድለቶችን እያረመ የሚጉለብትና የሚያድግ ነው። ስለዚህ አቶ ገብሩ ትርጉም የሌላቸው ቃላት ከመደርደር ከሌሎች ፌደራሊዝም ከገነቡት አገሮች ተሞክሮ ተነስተው ይህ እኛ ያላደረግነው ግን ማድረግ ያለብን ቁም ነገር አለ ብለው ማስቀመጥ ይገባቸው ነበር። አለበለዚያ ተራ አሉባልታ ከመሆን አይዘልም።

## 5. ሉዓላዊነትና የአንጀኞች ፖለቲካ፣

ቀደም ሲል ከህወሓት ተነጥሎ በወጣው አንጃ ሲስተጋባ እንደነበረው አሁን ደግሞ አቶ ገብሩ በመጽሓፋቸው ርዕስ ሳይቀር ሉዑላዊነት የሚል ቃል አስቀምጠዋል። ችግሩ ሉዑላዊነት ምንድነው? የሚለው ነገር በትንታኔ አስደግፈው አቅርበው ከዛ በመነሳትም ህወሓት/ኢህአዴግ ያጐደለውን መዘርዘር ይገባቸው ነበር። ነገሩ የፓለቲካ ይዘት ኑሮት ሳይሆን "እኛ አርበኞች፣ አገር ወዳዶች" የአንጃው ተቃዋሚ ወገን ደግሞ "አጐብዳጆች" ለሚለው ፈሊጥ የተነገረ ፖለቲካ መሳይ ስድብ ነው።

ለመሆኑ ሉዐላዊነት (sovereignty) ምንድ ነው? Jackson "Sovereignty in international relations signifies constitutional independence of other states"[1] ይላል አንድ አገር ከሌሎቹ አገሮች ሕገ መንግሥታዊ ነፃነት እንዳለው ነው የሚገልፀው። በመቀጠልም

[1] Simpson,"The Diffusion of Sovereignty: Self Determination in the Post-Colonial Age; in Sellers (ed.), 1996:53.

“Sovereignty is a legal, absolute and unitary condition; legal in that a sovereign state is not subordinate to another sovereign but is necessarily equal to it by international law… Absolute in that sovereignty is either present or absent. When a country is sovereign it is independent categorically; there is no intermediate condition… Unitary in that a sovereign state is a supreme authority within its jurisdiction”. [1]

ከላይ እንደምናየው ሃገራት በዓለም አቀፍ ሕግ ሉዐላዊነታቸው የተጠበቀ እንደሆነ፣ ከሕግ አንፃር ሁሉም ሉዐላዊ ሃገራት እኩል እንደሆኑ፣ ያልተሸራረፈ ሉዐላዊነትን የሚያረጋግጥና በአገራቸው ደግሞ ከፍተኛ የመወሰን ሥልጣን እንዳላቸው ያስረዳል። እንግዲህ ይህ የዓለም ዓቀፍ ሕግ ነው። ይህ ማለት ግን ዓለም ዓቀፋዊ ሁኔታና አካሄዱ ሁሉም ይህን ያንፀባርቃል ማለት አይደለም። ሃገራት ያላቸው ኢኮኖሚያዊ ይሁን ወታደራዊ አቅም የተለያየ ነው። በዘመነ ግሎባላይዜሽን ደግሞ በጥብቅ የተሳሰሩ እንደሆኑ ማየት ይቻላል። ስለሆነም በንድፈ ሃሳቡ የተገለፀው የሉዐላዊነት ትርጉም በዓለም ዓቀፍ ሁኔታ (international fact) የካርቦን ግልባጭ የመሆኑ ዕድሉ ያነሰ ነው።

ስለሆነም ሃገራት እላይ Jackson ያስረዳው ነገር እንዳለ ሆኖ ተግባራዊ ሲሆን ከፍተኛ የሚፈታተኑ አደጋዎች ስላሉት ሉዐላዊነትን ሰፋ አድርጐ አይቶ በተግባር ትርጉም ያለው ይዘት እንዲኖረው ያላሰለሰ ጥረት ይጠይቃል። ከላይ የተገለፁት እንዳሉ ሆነው የእድገት መንገድ ምርጫና የማስፈፀሚያው የፖሊሲዎች ባለቤትነት ከፍተኛ ትግል የሚካሄድበት ዓለም ነው ያለነው። የፖሊሲ ኪራይ የተንሰራፋበት ዓለም ከመሆኑ አንፃር ስለዲሞክራሲ ስናወራም መንግሥት በምርጫ ማቋቋም ብቻ ሳይሆን የህዝብ ሉዐላዊነትን በተሟላ መንገድ ማረጋገጥ ከፍተኛ ውጣ ውረድ የሚጠይቅ ቁም ነገር ነው። ስለሆነም ሉዐላዊነት ሰፊ ትርጉምና ይዘት ያለው ንድፈ ሃሳብ (concept) መሆኑን መገንዘብ የመጀመሪያው እርምጃ ነው።

---

[1] Robert H. Juckson, Quasi – States: Sovereignty, International Relations and the Third World, 1990:32.

እንግዲህ ከዚህ ተነስተን አቶ ገብሩ ስለሉዐላዊነት ሲያነሱ ሉዐላዊነትን በተሟላ (comprehensive) ትርጉሙ ሳይሆን ከኤርትራ በተፈጠረው የድንበር ችግር አንፃር ነው። በአብዛኛው ችግር ፈቺ በሆነ መንገድ ሳይሆን ምናልባት የፖለቲካ ጥቅም ይገኝበት ይሆናል ከሚል ጠባብ ቡድናዊ አስተሳሰብ ነው።

በህወሓት/ኢህአዴግ የአመለካከት ልዩነት የጀመረው ከኤርትራ ጋር ከተካሄደው ጦርነት በፊት ነው። ችግሮች እየተከሰቱ ሲሄዱ በተወሰኑ የአመራር አካላት ወደፊት በፍጥነት ለመጓዝ ችግሮችን መፍታት አዳር የማይባል ጉዳይ ነው የሚል አስተሳሰብ መንፀባረቅ ጀምሮ ነበር። የኤርትራ ጦርነት ባልታሰበበትና ባልተገመተ ሁኔታ ሲከሰት የግድ በድርጅቱ የነበረውን ችግር የመፍታቱ ፍላጐት ለሌላ ጊዜ እንዲተላለፍ የሆነበት ሁኔታ ተፈጠረ።

ለውጥ በሚፈልገው ወገን በድርጅቱ ያለው ችግር የፀረ-ዲሞክራሲና የአለአግባብ የመጠቀም ዝንባሌ ማለት ሙሰኝነት እየገነነ መጥቷል። ከዚህ አዘቅት የምንወጣበት መንገድ ተወያይተን መፈለግና ማስቀመጥ አለብን፣ ጥገኛ ዝቅጠቱ ከቀጠለ በድርጅቱም በሃገሪቱም ከፍተኛ ችግር ስለሚፈጥር ተሎ ከዚህ መውጣት ይኖርብናል። ችግሩ የውስጣችን ነው የሚል ሲሆን ድርጅቱን ጥሎ የሄደው ቡድን ደግሞ የችግሮቹ ምንጭ የኤርትራ መንግሥትና ለእርሱ ያጎበደዱ የአመራር አባላት ናቸው በሚል ክርክሩን ተያያዘው።

እንግዲህ እንደምናስታውሰው በአንድ በኩል በውስጣችን የነበረው በይደር የተላለፈው ችግር በሌላ በኩል ደግሞ የኤርትራ መንግሥት ያለአግባብ የመጠቀምና የመዝረፍ ፍላጐቱን ሊጭንብን በከፈተው ጦርነት ሁኔታዎች በጣም በሚያስቸግር ሁኔታ የተመሰቃቀሉ እንዲሆኑ አድርጓል። የኤርትራ መንግሥት ቀደም ብሎ የነበረው በኢኮኖሚያዊ ስርቆት ሊገለፅ የሚችል ተግባሩ ሲገደብበት በኋላም የገንዘብ ልውውጥና ሁለቱ ገንዘቦች እኩል በሁለቱም ሃገሮች የመስራት ሁኔታ ሰማይና መሬት በሚራራቁ የሞኒተሪና የፊሲካል ፖሊሲዎች ባሉበት ጨርሶ እንደማይቻል ሲነገረው የባድመ ምክንያት (pretext) በመፍጠር ወረራውን እንደጀመረው የሚታወቅ ነው።

የኢትዮጵያ መንግሥት የኤርትራ ሕገ-ወጥ ወረራ በአስቸኳይ እንዲቀለበስና የኤርትራ መንግሥት የይገባኛል ጥያቄ ካለው በሕግና በሕግ ብቻ እንዲጠይቅ፣ ችግሩን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ያደረገው ሙከራ የኤርትራ መንግሥት በእብሪት የሰላም መፍትሄውን አልቀበልም፣ ኢትዮጵያ አሁን በብሄርና ብሄረሰብ ልዩነት የተከፋፈለችና የተዳከመች ነች፣

ፍላጐቱን እምጭነው ጊዜው አሁን ነው በማለት አሻፈረኝ ብሎ በጦርነቱ እንደገፋበት የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው፡፡ ይህ የኤርትራ መንግሥት እብሪት በሰላም የመፍታቱ ሁኔታ ዝግ እየሆነ በመጣበትም ሁኔታ የኢትዮጵያ ህዝብ እንኳን ለኢትዮጵያውያን ለሌሎች ወዳጆቻችን በሚያኮራ መንገድ ባንድነት ቆሞ የኤርትራ መንግሥትና ሠራዊት አይቀጡ ቅጣት ቀጥቶ ከወሳኝ የኢትዮጵያ ግዛቶች እንዲባረር ተደረገ፡፡

ይህ ከባድ ቅጣት የኤርትራ መንግሥት የአፍሪካ መሪዎች ከጦርነቱ በፊት ሰላም ለማውረድ ያቀረቡለት The OAU Framework Agreement ከጦርነት በፊት እንዳላጣጣለውና የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን የማይረባና የጀርባ አጥንት የሌለው (fickle organization) እንዳላላው Framework Agreement አንደተቀበለና ለአፈጻጸሙ እንደሚወያይ አስታወቀ፡፡ የኤርትራ መንግሥት በጦር ሜዳ ምንም ለውጥ እንደማያመጣ በተፃራሪው ግን ነገሩ እየጠበቀበት እንደመጣ ሲገነዘብ የአፍሪካ መሪዎች ማመፀን ጀመረ፡፡ የአፍሪካ መሪዎች በ35ኛው ስብሰባቸው የFramework Agreement የአፈፃፀም modalities አፀደቁ፡፡ እዚህ ያሉት ቁምነገሮች አንደኛው የኤርትራ መንግሥት ግንቦት 1990 ከወረረው ቦታ ሠራዊቱን እንዲያወጣ ሲሆን ሌላው የኢትዮጵያ መንግሥትም ከጥር 1991 በኋላ ከተቆጣጠረው የኢትዮጵያ ግዛት ካልነበሩት አካባቢዎች ሰራዊቱን እንዲያስወጣ ናቸው፡፡ በመቀጠልምThe Technical Arrangements for the Implementation of the OAU Framework Agreement and its Modalities ተዘጋጅቶ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት፣ የተባበሩት መንግሥታት፣ የአሜሪካ መንግሥትና ሌሎች ተሳታፊ ሃገሮች ድጋፍ አግኝቶ ተዘጋጀ፡፡

ቴክኒካል አሬንጅመንትስ ከተዘጋጀ በኋላ ብዙ የማብራሪያ ጥያቄዎችና የማስተካከያ ሃሳቦች እንደ ድርጅት በመንግሥት በኩል አቅርበን ከወራት ድርድር በኋላ Consolidated Technical Arrangement የሚል ዶክሜንት ተዘጋጀ፡፡[1] በመጨረሻ የተዘጋጀው ዶክሜንት የተወረሩትን አካባቢዎች ጨርሶ የኤርትራ መንግሥት እንዲለቅ የሚያስገድዱና የቀድሞው status quo የሚመልስ በመሆኑ ከዚህም በላይ የሚፈለግ ቢኖርም ጦርነቱ በፍጥነት ቋጭተን ፊታችን ወደ ልማትና ወደ አገር ግንባታ ለማዞር ለምንፈልግ የአመራር አባላት የቀረበውን ዶክሜንት እንቀበል የሚያሰኝ ነበር፡፡ እዚህ ላይ አመራሩ ውስጥ ከፍተኛ ልዩነት አስነሳ በአንድ በኩል ጦርነቱ ይብቃን ወደልማትና ወደ አገር ግንባታ ቀልባችን ይዞር የሚልና በሌላ በኩል ጦርነቱ እስከ መጨረሻ አስቀጥሎ የኤርትራን መንግሥት ሙሉ

[1]For details, Addis Alem Balema, Democracy and Economic Dvelopment, 2014: 241-294.

በሙሉ ለማንበርከክና እንደ አሰብ የመሳሰሉትን ደግሞ በሃይል ቆርጦ ወደ ኢትዮጵያ የማምጣት ፍላጐት ተራመደ፡፡ በዚህ ወቅተ ነበር አቶ ገብሩና ጓደኞቹ "ኢኮኖሚው ተንገራግጮ እስኪቆም ድረስ እንዋጋለን" በማለት የጦርነት ጉትጉታውን ስራዬ ብለው ተያያዙት፡፡ ውይይቱ ቀጥሎ ሰላማዊ መፍትሄ ማስቀደም ይገባናል፡፡ ጦርነቱም በፍጥነት መቋጨት አለበት የሚለው ወገን በድምፅ ብልጫ ተሸንፎ፤ ይህ ጦርነቱ አልቆ ወደ ድርጅቱ ችግር መፍታት ብሎም ወደ ልማት መሰማራት ፍላጐት ያልነበረው ቡድን ያሸነፈበት፣ በኤርትራም በኩል ለሰላም የቆመ ሃይል በሌለበት ሁኔታ ሁለተኛው ጦርነት የሚካሄድበት ሁኔታ ተፈጥሮ በሁለቱም ወገን በሺዎች የሚቆጠሩ የወጣቶች ህይወት አልፏል፡፡ አቶ ገብሩ በገፅ 318 "ሻዕቢያዎች አይቀጡ ቅጣት ተቀጥተው እንዲፍረከረኩ ያልፈለገው መለስ፣ ከጐኑ የተሰለፉት የህወሓት ማዕከላይ ኮሚቴ አባላትና አንዳንድ የጦር አዛዥችም ለዚህ ለኢትዮጵያ የተሟላ የጦር ሜዳ ድል ማጣት ምክንያት መሆናቸውን ታሪክ ይመዘግበዋል፡፡" ይላሉ፡፡

አቶ ገብሩ ሁሉም ነገር "ዘራፍ" በማለት የሚፈፀም ይመስላቸዋል፡፡ መጀመሪያ ማስተዋል ያለብን ኢትዮጵያ በ10 ዓመታቱ በአምስት በመቶ በማደግም ቢሆን ያስገኘችው የኢኮኖሚ አቅም ነው ጦርነቱን የተሸከመው፡፡ በፈራው ሃብት ነው የጦር መሳሪያ የተሸመተው፡፡ ይህ ግን የራሱ ገደብ (limitation) አለው፡፡ ጦርነት ሰው ቢሰበሰብም ያለ ሃብት (resource) ማስኬድ አይቻልም፡፡ በተነፃፃሪ ካዩት ሻዕቢያ ገና ጦርነቱ እንደተጀመረ ይህ ነው የሚባል የሚያንቀሳቅሰው ሃብት ስላልነበረው ነው ወገቤን ያለው፡፡ "ተፃወሩ" ማለትም እንደምንም ተሸክማችሁ ተዋጉ ወደ ማለት የገባው፡፡ ይህ ልዩነት የተፈጠረው ኢህአዴግ በተከተለው የኢኮኖሚ ፖሊሲና ለተግባራዊነቱም ወገቡን አጥብቆ ስለተረባረበ ነው፡፡ የኢኮኖሚ ጉልበት ማለትም የሚቀርበው የlogistics አቅም ያለው ወሳኝነት ሲገልፅ Napoleon "An army marches on its stomach". አለ ይባላል፡፡

ሌላው ጦርነቱ እንዲቆም የተደረገው እንዲያው በግለሰብ ፍላጐት ተደርጐ መቅረቡ ከሓቅ የራቀ ነው፡፡ በወቅቱ የነበረው Command Post ከፊት የነበሩትን የጦሩ አዛዦች ቅኝት አድርገው ወደፊት ስለመቀጠሉ ሁኔታ አስተያየት እንዲሰጡ በጠየቀው መሠረት የጦር አዛዦቹ ሁኔታውን አይተው ተወያይተው፣ ውሳኔ ላይ ደርሰው ባንድ ቃል ነበር የውሳኔ ሃሳብ ያቀረቡት፡፡ ከዚህ በመነሳት ኮማንድ ፖስቱም ባንድ ድምፅ ጦርነቱ እንዲቆም የወሰነው፡፡ ይህም በየደረጃው ሂዶ በኢህአዴግ ምክር ቤት ታይቶ ትክክለኛነቱና ተቀባይነቱ ተረጋግጧል፡፡ እንግዲህ ለነገሩ ጦርነቱ የቆመው መቆም ስለነበረበት ነው፡፡ ጦርነቱን ሲመሩ

የነበሩ የጦር መሪዎች ተሰብስበው ጦርነቱ መቀጠል አይቻልም ካሉ የባለሙያ ድምዳሜ መቀበል አስፈላጊ ይመስለኛል። ለነገሩ እነ አቶ ገብሩ ራሳቸውን የሁሉም ጉዳይ ባለሙያዎች አድርገው ያስቡ ስለነበርና ፍላጐታቸው ከነበረው ተጨባጭ ሁኔታ (reality) ይጋጭ ስለነበር አልተቀበሉትም። ይህን የውሳኔ ሃሳብ ያቀረቡ ጀግኖች integrity ጥያቄ ውስጥ ማስገባት ግን ዕብደት ይመስለኛል።

ሌላው የኤርትራ መንግሥት ፀረ-ህዝብ በመሆኑ ኢትዮጵያውያንን ማፈናቀል ስራዬ ብሎ ተያይዞት እንደቆየ ይታወቃል። ተግባሩ በጣም የሚያሳዝን ቢሆንም በህዝባዊነትና በመግባባት ችግሩ እንዲፈታ የኢትዮጵያ መንግሥት ሲሰራ ቆይቷል። ጦርነቱ ሲጀምርም ያው የኤርትራ መንግሥት በሽታ አገርሽቶበት በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ማባረረ ጀመረ። በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ግን የተወሰደው አቋም ከህዝብ ጋር የሚያጣላን ነገር የለም። ዓላማችንም የህዝብ ነው። ሆኖም በኤርትራ መንግሥት የአደረጃጀት ማለትም በአመራር የነበሩትና በህቡእ ደግሞ የተደራጁትን የለየላቸውን የሻዕቢያ አባላትና ደጋፊዎች የፀጥታ አደጋ የማድረስ አቅማቸው የማይናቅ ስለሆነ እኒህን ብቻ ለይተን እንለካቸው ነበር። ይህ አቋም በአግባቡ መተግበር ጀመረና ከዛ በኋላ በነ አቶ ገብሩና በወቅቱ ኢህአዴግ ጽህፈት ቤት በነበሩ የአመራር አካላት ስራው ተወስዶ (hijack ተደርጐ) መላውን ትውልደ ኤርትራ አቅማቸው በቻለው መጠን ማባረር ተያያዙት። አሮጊት፣ ሽማግሌ፣ ህፃናት ወዘተ... ባልለየ የቂም በቀል (revenge) በሚመስል አካሄድ አስፈፀሙት። ባጋጠማቸው ጠንካራ ተቃውሞ ትንሽ ጋብ ወደ ማለት ሄደ እንጂ በእነሱ አካሄድ ቢሆን ኑሮ ከፍተኛ ጉዳት (havoc) ይፈጠር ነበር።

ይህ ነው እንዲህ የአቶ ገብሩና ጓደኞቻቸው የአርበኝነት መለያ፣ እስከአሁንም አቶ ገብሩ እኮራበታለሁ ብለው የሚያወሩት። ይህን የተቃወመ ደግሞ “አገር በመክዳት ወንጀል” መክሰስ የጀመሩት። ይህ በጦርነት ጊዜ በሌሎች አገሮች አይፈፀምም አይደለም። በጦርነት ጊዜ ጀብደኞችና demagogues (ህዝቡን በስሜትና በቂም በቀል መንዳት ስራዬ ብለው የያዙ ፀረ-ሰላምና ፀረ-ህዝብ ሃይሎች) ናቸው እንደልባቸው መፈንጪያ የሚያገኙት። በሁለተኛ ዓለም ጦርነት አሜሪካኖች ከ110,000-120,000 Japanese-Americans ልጆቻቸውን ወደ አሜሪካ ሠራዊት ልከው ውድ ህይወታቸውን ከፍለውም በመከፈል ላይ የነበሩትንም ጭምር፤ ከ62 ከመቶ በላይ የሆኑት የአሜሪካ ዜጎች እያሉ በካምፕ አጉረው ያሰቃዩበት ሁኔታ ነበር። ይህ ሁኔታ በኋላ አሜሪካኖች በታሪካቸው ጥቁር ነጥብ እንደሆነ ተቀብለው

ለተበደሉት ይቅርታና ካሳ የከፈሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል። የእኛዎቹ ጀብደኞች ግን ከሁለት አሥርት ዓመታት በላይ ለህወሓት/ኢሕአዴግ ህይወታቸውን ለመስዋዕት አዘጋጅተው ከእነሱ ጐን የታገሉ ታጋዮችን ሳይቀር የኤርትራ ትውልድ አለው የለውም ወደሚል በጣም አሳፋሪና አስቀያሚ ደረጃ ወረዱ። ለአንባቢው ግልፅ እንዲሆን ግን አንድ ምሳሌ ላቅርብ። ነጋሲ ወላይ ነባር ታጋይና የጦር አዛዥ፣ አባቱ አቶ ወላይ ተክለሃይማኖት የታወቁ የህወሓት ሚሊሻ፣ አባትና ልጅ በትውልድ ኤርትራውያን ሁለቱም ደግሞ ባድመ ላይ በጀግንነት የኢትዮጵያን ድንበር አናስደፍርም ብለው ተሰውተዋል። ይህ ነው የዓላማ ፅናትና አገር ወዳድነት። እንደኒህ የመሰሉ ህይወታቸውን የሰጡና በህይወትም ያሉት ከፍተኛ አስተዋፅኦ የነበራቸውና ያላቸው ታጋዮችን ነው ለማሸማቀቅ የተሞከረው። አሁንም አላፈሩበትም፤ እነ አቶ ገብሩ በሰሩት ፀረ-ህዝብ ስራ "ይኮሩበታል"። ከአንድ ህዝብ መወሰድ አይደለም ወሳኙ፤ ዋና ቁምነገሩ የፖለቲካዊ መስመር ሰልፉና ለህዝብ መብትና ጥቅም ሁሌም በፅናት መቆሙ ነው።

እነዚህ ሰዎች በጦርነት ወቅት በህዝብ ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎች ጥንቃቄ እንደሚጠይቁ አልገባቸውም። በጦርነት ሙቀትና ከገደብ የወጣ ስሜት (hysteria) ውስጥ የሚወሰዱ እርምጃዎች የረዥም ጊዜ ጠባሳ ሊተው ይችላሉ። በህዝብ ላይ የሚፈፀም ምክንያታዊ ያልሆነ (irrational) እርምጃ ግን መዘዙ ብዙ መሆኑን መረዳት ይገባል። ለማንኛውም ኢህአዴግ እንደ ድርጅት የተሰራውን ፀረ-ህዝብ ሥራ ኮንኖ በሁለቱ ህዝቦች መሃከል ቅራኔ መኖር እንደሌለበት፤ እንደወንድማማቾችና ጐረቤታሞችም የኤርትራ መንግሥት የፈጠረው ሳንካ አብቅቶለት ለሰላም፣ ለልማትና ለዕድገት አብሮ የመስራቱና የመታገሉ እድል ሩቅ እንደማይሆን አስቀምጧል። ለዚህም አንድ ማሳያ መሆን የሚችለው የፖሊሲው ውጤት የሆነው በርካታ ኤርትራውያን ወገኖች አሉን ብለው በጦር ሠራዊቱና በፈንጂ የታጠረውን ድንበር ተሻግረው ወደ ኢትዮጵያ እየጐረፉ ያሉት። ዋናው ቁም ነገር ያለፈው የተፈፀመ ስህተት መደገም የለበትም ተብሎ እንደማስተማሪያ መወሰድ ይኖርበታል።

እነ አቶ ገብሩም ቢሆኑ ሁሌም በኤርትራ ይሁን በኢትዮጵያ መንግሥት የተፈፀመ ስህተትን በሚያሰለች መንገድ እያወራን መቀጠል የለብንም። ኢትዮጵያ አሁን ከጐረቤት አገሮች በጋራ ጥቅምና በመከባበር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እየገነባች ነው። አብሮ የመልማት፣ ኢኮኖሚያዊ መተሳሰሩ እንዲጠነክር፣ ሰላም እንዲሰፍን የዘወትር ህልማችን መሆን አለበት። ይህ ነው ካንድ የአገር አመራር (leadership) የሚጠበቀው። Lord Palmerstone ያለው

ቁም ነገር የተላበሰ አባባል አለ፡፡ “We have no eternal allies and we have no perpetual enemies. Our interests are eternal and perpetual, and those interests it is our duty to follow”. Palmerstone ዘለአለማዊ ወዳጆችና የሁሌም ጠላቶች የሉንም፡፡ የእኛ ጥቅሞች ዘለአለማዊና ቀጣይነት ያላቸው ናቸው፡፡ የእኛ ተልዕኮ ደግሞ እነዛን ጥቅሞች ማስጠበቅና ማስፈፀም ነው ይላል፡፡ በተመሳሳይ የእኛም የአገር ጥቅም ማስከበር ነው ተልዕኳችን፡፡

ወደ ህወሓት/ኢህአዴግ የአመራር ረዥም ውይይትና በተለመደው የድርጅት ባህል አለመገባደድ ስንመለስ፣ የሆነው ነገር ዲሞክራቲክ አፈጻጸም አልነበረውም፡፡ ዲሞክራሲ የብዙሃን አገዛዝ ነው፡፡ ይህ ማለት ውሑዱን መብታቸው ይጠበቃል፣ ይደመጣሉ ነው፡፡ የውይይቱ ጭብጥ በየትኛውም ምሳሌዎችና ማብራሪያዎች ቢታጀብም ፀረ ዲሞክራሲያዊ አሰራርና አላግባብ የመጠቀም ፍላጐትና ተግባር እየጐለበቱ ነው፡፡ እነዚህ መወገድ አላባቸው፡፡ ሌላው ወገን ከላይ እንደገለጽኩት ከእነሱ ውጭ ያለው አመራር ለኤርትራና ለውጭ ሃይሎች አጐብዳጅና ተንበርካኪ ነው የሚሉ ናቸው፡፡ የቀረቡት ፅሑፎች ብዙ ሰው ስላያቸው ይዘታቸው ምን ያህል የውይይቱን ደረጃ ጠብቀዋል እንዳለ እተወዋለሁ፡፡ አንደኛ ውይይቱ በሰፋት ተካሂዶ ሁሉም ተጠቦ፣ ተጨንቆ የቻለውን አጥንቶ ነው አቋም የወሰደው የሚል እምነት አለኝ፡፡ አቶ ገብሩ ከሳቸው ቡድን ውጭ ያለው አመራር በአቶ መለስ ቤት ግብዣ እየተንበሸበሸ ተደለለ የሚለው አባባል ምን ያህል እራሳቸውን አሁን ካሉበትም ለምን ዝቅ እንደሚያደርጉ አልገባኝም፡፡ ብዙ ነገር የሚያውቅ አመራር “በአቶ መለስ ቤት ግብዣ ተደለለ” ቢሉ አገር ይስቃል፡፡ ለእውነትም ሲባል ውይይቱ እስኪያልቅ ድረስ ሰው ተጨንቆና ተጠቦ በነበረበት ወቅት ለድግስ ጊዜ ነበረው የሚል ውሃ የሚቋጥር አይደለም፡፡ ሁለተኛ ዋናው ቁም ነገሩ በድርጅታችን ባህል ድምፅ ተሰጥቶ ከተቆጠረ በኂላ ሁሉም ወደ ጦርነት ሳይቀር አብሮ ይዘምታል የሚለው በስተመጨረሻ ወረወራችሁት፡፡ ካሸነፍን እናሸንፋለን፣ ከተሸነፍን ደግሞ በውሳኔው አንገዛም የሚል ዲሞክራሲ፣ መብትና ግዴታ ማክበርና ማስከበር በምን መነፅር ታይቶ ነው፡፡ ከዛ በኂላ አንዱን መድረክ ስትረግጡ ሌላው ስትደግሙ ራሳችሁን ከብዙሓን የድርጅት አባላት ነጠላችሁ፣ ማንነታችሁም ተጋለጠ፡፡

ሦስተኛ “አባረሩን” የሚለው ነገር ረግጠህ ከወጣህ በኂላ የራስህን ቡድን አደራጅተህ ጉባኤ ከተቀመጥክ የሚከተለውን ነገር ግልፅ ይመስለኛል፡፡ ሁለት የሥልጣን ማዕከላት (power centers) በዚህ አገር ይሁን በአጠቃላይ በሌሎች ሃገራትም ቢሆኑ መቀጠል አይችሉም፡፡

የግድ አቧራው ዝግ እስኪል እንኳን ውሑዳኑን ራሳቸውንና ሃገርን እንዳይጐዱ ማገድ ተገቢ ይመስለኛል። ከዛ አንጃው ያወጣው መግለጫ የቤተመንግሥት ቡድን "የኢምፔሪያሊስት ቡችላ" ወዘተ... የሚል ትርጉሙ ግብቶአቸው ነበር? አሁን ደርሰው አቶ ገብሩ "ሊበራል ዲሞክራት" ነኝ እያሉ ነው። ማን የሚያራግበው ideology ይመስለዎታል? ስለዚህ "እጅዎን ሰጡ" ልበል? ለነገሩ ድሮ የአንጃው አባላት የነበሩ በርከት ያሉት አሁን ያለውን የአገሪቱን የለውጥና የእድገት ሂደት ጠንካራ ይሁን ደካማ ጐኑን ሚዛናዊ (rational) በሆነ መንገድ እያዩ ነው የሚል ከግምት ያለፈ አመለካከት አለኝ።

በማጠቃለል አቶ ገብሩ ስለሉዐላዊነት በየዘመቱበት ያወራሉ። ምናልባት እኔ እንዳደረኩት ንድፈ ሓሳቡን አስቀምጠው ከዚህ ጐደለ እዛ አነሰ ቢሉ መልካም ነው። አለበለዚያ የኢትዮጵያ መንግሥትን በሉዓላዊነት አለማስከበር መክሰስ ከቀጠሉ ዓለም ይስቅቦዎታል። የኢትዮጵያ መንግሥት የሚከተለው ልማታዊ ዲሞክራሲ የፖሊሲ ኪራይን (policy rent) ይቃወማል። ሊበራል ዲሞክራሲ ከሚለው በተለየ የመንግሥትን የተመረጠና አስፈላጊ የሆነ ጣልቃ ገብነትን ይሰብካል፣ ይፈፅማል። እርስዎና ድርጅትዎ ናቸሁ "ይህ ይሸጥ ያ ይለውጥ" እምትሉት። በተፈጥሮ ሞኖፖሊ የሆኑ የአገር ሃብቶች ስትሸጡ  የሚገዛው አሁን ያለው ያልጠነከረው የአገር ውስጥ ባለሃብት አይደለም። የውጪ corporate capitalism ነው። ይህ ታዲያ በምን ሂሳብ ነው ሉዓላዊነትን ማስከበር የሚሆነው? ሉዐላዊነት ምን ያህል ሰፊ ትርጉም እንዳለው ከላይ አስቀምጫለሁ። የእርስዎ ሉዐላዊነት ጐደሎም ነው፤ ከጐድለቱ በላይ ደግሞ የሚጨበጥ እውነታ የለውም። ስለዚህ እኔ እምመክርዎ የዚህ የተሳሳተ ሃሳብ ተጋሪ የሆነ ሁሉ ወደ ውስጥ መጀመሪያ ይይ፣ የጐደለ ነገር አለ፣ አይ ዘፈኑን እቀጥልበታለሁ የሚል ደግሞ ይህ አገር ትልቅ አገር ነው "ሁሉንም" ያስተናግዳል::

## 6. ኤርትራ ወይስ አሰብ፣

የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ኤርትራ ለኢትዮጵያ እንድትሰጥ ከፍተኛ ትግል እንዳደረገ ይታወቃል። በተባበሩት መንግሥታት የነበረው የሃሳብ ልዩነትና ፍጭትም በዝርዝር ማየት ይቻላል። ከብዙ ክርክር በኂላ የተባበሩት መንግሥታት የኤርትራ ልዩ ማንነት (identity) ተቀብሎ ነው በፌዴራል ሥርዓት ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቆራኝ የወሰነው። ትላልቆቹ አገሮች ከራሳቸው ጂኦ-ፖለቲካል ጥቅም ተነስተው የተለያዩ መፍትሄዎች የሚልዋቸውና የክርክር አግባቦችም ተጠቅመዋል። አሜሪካም አቶ ገብሩ እንደሚሉት ለኢትዮጵያ አዝና

ሳይሆን ከራስዋ ጥቅም እንደሆነ ለማወቅ የሚያዳግት አይደለም። የፌዴሬሽን ውሳኔው እንደተሳለፈ የአሜሪካኑ የተባበሩት መንግሥታት ተወካይ ቀጥሎም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበረው John Foster Dulles እንዲህ ብሎ ይገልፀዋል። “From the point of view of justice, the opinion of the Eritrean people must receive consideration. Nevertheless, the strategic interest of the U.S in the Red Sea Basin and world peace makes it necessary that the country be linked with our ally Ethiopia.” ከላይ እንደተገለፀው Dulles ከፍትህ አንፃር የኤርትራ ህዝብ ፍላጎት ሚዛን ሊሰጠው ይገባል። ሆኖም አሜሪካ በቀይ ባህር አካባቢ ካላት ሃገራዊ ጥቅም ይሁን ከዓለም ሰላም ቀመር አገሪትዋ (ኤርትራ) ከወዳጃችን ኢትዮጵያ ጋር እንድትቆራኝ መርጠናል ነው የሚለው። እንግዲህ አሜሪካኖች ውሳኔውን ሲደግፉና የእነሱ ተከታዮች ከእነሱ ጋር ድምፅ እንዲሰጡ ሲገፋፉ በዛ ወቅት የነበረው የአሜሪካ ጥቅም፣ የአረቦችና የእሥራኤል ፍልሚያ፣ ከሶቭየት ሕብረት ጋር እየጀመረ የነበረው ፍጥጫ ዋናው መነሻ ነበር። ስለሆነም ያኔ የነበረው ድጋፍ ለአሁኑ ከኤርትራ መሬት ቆርሶ ለመውሰድ የአሜሪካ ድጋፍ መሻት ቢያንስ የዋህነት ነው።

Resolution 390 (V) of 2 December 1950 በ46 ድጋፍ፣ በ10 ተቃውሞና በ4 ድምፀ ተዐቅቦ ሲፀድቅ የ1900፣ 1902፣ 1908 ዓ.ም. ውሎች በሪዞሊሽን ፈርስዋል የሚሉ አባባሎች የሕግ መሰረት ያላቸው አይደሉም። ውሎች (treaties) በሪዞሊሽን ይፈርሳሉ ወይም ይተረጐማሉ የሚል አባባል እንዴት እንደሚቻል ግልጽ አያደርጉም። አቶ ገብሩ ከዚህ በፊት የሆነበት አገር ምሳሌም (precedence) ማቅረብ አይችሉም። ከዚህ በላይ ግን Resolution 390(V) ያደረገው ነገር ካለ በነዛ ኮሎኒያል ውሎች የተከለለችውን ኤርትራ እንዳለች እንደ ፌደራል አካል (federal entity) ወስዶ ነው ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትቆራኝ የወሰነው። ይህም ውሳኔ የተባበሩት መንግሥታት ለመጀመሪያ ጊዜ አስፈፃሚ ኮሚሽነር ሰይሞ ሊተረጉመው ሞክሯል። የResolution 390(v) የመጀመሪያዎቹ ሰባት ፓራግራፎች ማለትም የኤርትራ መንግሥት ይዘት፣ የፌዴሬሽኑ መመስረቻ ሃሳቦችና የሰብዓዊና የፖለቲካዊ መብቶች የሚዘረዝሩት Federal Act ተብለው ንጉሰ ነገስቱ እንዲያፀድቋቸው ይጠይቃል። Paragraph 8 “paragraphs 1-7 inclusive of the present resolution shall constitute the Federal Act which shall be submitted to the Emperor of Ethiopia for ratification”. ይላል። በሪዞሊሽኑ መሰረትም የኤርትራ ፓርላማ በ28 April

1952 በኦፊሴል ከተከፈተ በኋላ የተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽነር ያቀረበው ረቂቅ ሕገ መንግሥት ማለትም በሪዞሉሽኑ የተዘረዘሩትን Federal Act የተባሉትን ጨምሮ 10 July 1952 አጽድቆታል። ንጉሰ ነገስቱ የኤርትራ ሕገ-መንግሥት በ11 August 1952 ዓ.ም፣ የፌደራል ሕጉ (Federal Act) ደግሞ በ11 September 1952 ዓ.ም. ፈርመው አፅድቀዋል።

ንጉሰ ነገስቱ በፈረሙበትና ባፀደቁት የኤርትራ ሕገ-መንግሥት ኤርትራ የትኛው ነው የሚል ግልጽ መልስ ይሰጣል። Article 2 Territory of Eritrea በሚለው አንቀጽ ይህ በግልጽ ተቀምጧል። "The territory of Eritrea, including the islands, is that of the former Italian colony of Eritrea" ይላል። ከላይ እንደተጠቀሰው አንቀጽ 2 የኤርትራ ግዛት ብሎ "የኤርትራ ግዛት ደሴቶችን አጠቃልሎ የቀድሞው የጣልያን የኤርትራ ቅኝ ግዛት ነው" ይላል። እንግዲህ በእነዛ አንድንድ ሰዎች ፈርሰዋል ባልዋቸው ውሎች (treaties) የተፈጠረችው ኤርትራ እንዳለች ግዛቶችዋ እንደተጠበቀ ነው ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን የተሳሰረችው። ስለሆነም አሁን የማይጨበጡና ትርጉም የማይሰጡ ምክንያቶች ብንዘረዝር ራስን ከማሞኘት በላይ የሚያዛልቅ አይሆንም።

ንጉሰ ነገስቱም ይሁን የኢትዮጵያ መንግሥት በተባበሩት መንግሥታት የፀደቀውን የFederal Act በውስጣቸው አልተቀበሉትም ነበር። ስለሆነም ከመጀመሪያውኑ ጀምሮ የተከተሉት መንገድ ፌዴሬሽኑን አፍርሰው ኤርትራን አንድ ጠቅላይ ግዛት የማድረግ መንገድ ነበር። ብዙ ሳይቆይ 1956 ዓ.ም. የኤርትራ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 38 ያስቀመጠውን የኤርትራ ኦፊሴል ቋንቋዎች ትግረኛና አረብኛ የሚለውን በመሻር አማርኛ የኤርትራ ኦፊሴል ቋንቋ እንዲሆን የኢትዮጵያ መንግሥት አዘዘ። ከዛም የኢትዮጵያ መንግሥት የኤርትራ ባንዲራ እንዳይውለበለብ፣ የኤርትራ መንግሥት የሚለውም በ"ኤርትራ አስተዳደር" እንዲተካ፣ ከዛም ይባስ ብሎ እ.ኤ.አ በ1959 የኢትዮጵያ ሕግ በኤርትራ እንዲሰራና በግድ እንዲፈፀም ተደረገ። ይህ ሁሉ ሲሆን የፌደራል ሥርዓቱን መቀጠል የሚደግፉ ወገኖች የኢትዮጵያ መንግሥትና የኢትዮጵያ መንግሥት ተወካይ ጣልቃ ገብነት ሲቃወሙ የንጉሱ አማች ራስ አንዳርጋቸው መሳይ ይህን ብለው ነበር።

> "Neither I nor my assistants would understand, nor did anyone explain to us the meaning of the allegation that the Office of H.I.M.'s Representative has intervened in the internal affairs of Eritrea and has

attempted to corrupt the faith of the Members of the Assembly. In any case there is no internal or external affairs as far as the Office of H.I.M.'s representative is concerned and there will be none in the future. The affair of Eritrea concerns Ethiopia as a whole and the Emperor". [1]

በጥቅሱ እንደተገለፀው ራስ አንዳርጋቸው መሳይ አንደኛ የንጉሰ ነገስቱ ተወካይ ጽ/ቤት በኤርትራ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብቷል የሚለውም ይሁን የኤርትራ ምክር ቤት አባላትን ለመደለልና በሙስና ለመያዝ ሞክሯል የሚሉት እሳቸው ይሁን ረዳቶቻቸው ፍፁም እንደማይገባቸው። ሁለተኛ እንደሳቸው ከሆነ የውስጥ ጉዳይ ወይም የውጭ ጉዳይ የሚባል ነገር እንደሌለና እንደማይኖርም የኤርትራ ጉዳይ በአጠቃላይ ኢትዮጵያን ይሁን ንጉሰ ነገስቱን እንደሚያገባቸው ነው እያረጋገጡ ያሉት።

ይህ ብቻ አይደለም የንጉሰ ነገስቱ ቀኝ እጅና የቅርብ አማካሪያቸው ልዑል ራስ ካሳ ሃይሉ እነ ፀሐፌ ትእዛዝ አክሊሉ ሃብተወልድ ፌደሬሽኑ እንዳይፈርስ ለኤርትራ ብቻ ሳይሆን ሌሎች በወቅቱ በሞግዚት አስተዳደር ይሁን በቅኝ አገዛዝ የነበሩ የአካባቢያችን ህዝቦች የኤርትራው ሙከራ (experiment) ከሰራ ወደኛ ሊሳቡ ይችላሉ ብለው በተከራከሩበት ወቅት ከዚህ በታች ያሉትን ስናይ የነበረው አስተሳሰብ ምንኛ ኋላ ቀርና ቀጥሎ ለመጣው ጦስ መነሻ እንደሆነ ማየት እንችላለን።

> "....የውጭ ጉዳዩን አክሊሉን በጣም አደራ የምለው የኢትዮጵያ አንድ መሆን ከሁሉ በላይ ትልቅ ነገር መሆኑን ነው። ..... በኤርትራ ነገር የሆነው ሲገርመኝ አሁን ደግሞ የመቅደሾም የሀርጌሣም ሱማሌዎች በኤርትራው ዓይነት መተዳደሪያ (ፌዴሬሽን) ወደ እኛ እንዲመጡ መድከም አለብን ብሎ አክሊሉ ሲናገር ሰማሁ። .... ሱማሌዎች ወደ እኛ መምጣት ካመለከቱ ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያ ሆነው ነው እንጂ መተዳደሪያቸው ግማሽ በግማሽ ሆኖ አይደለም። ግማሽ በግማሽ የሆነ መተዳደሪያ ታላቋን ኢትዮጵያን ስለማይጠቅማት እዚያው አሉበት ይኑሩ...."[2] (ልዑል ራስ ካሳ ሃይሉ)

[1] Ras Andargachew Messay quoted in Tekeste Negash, 1997:102
[2] ዘውዴ ረታ፣ የኤርትራ ጉዳይ፣ 1992፡446.

ፀሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሲከራከሩበት የነበረው ቁምነገር የኤርትራ ፌደራል ሥርዓት በአግባቡና በተፈለገው መንገድ ከቀጠለ በወቅቱ በቅኝ ግዛት ይሁን በሞግዚት አስተዳደር ስር የነበሩት ጅቡቲና ሶማሊያ ሪፈረንደም ሊካሄድ ስለሚችል በኤርትራው መንገድ ለመዋሀድ ኢትዮጵያን ሊመርጡ ይችላሉ ከሚል ነው። ነገሩ የኤርትራም እንደተባለው አልተቃናም። በ1960 ዓ.ም.ሶማሊዎችም የራሳቸውን መንግሥት መሰረቱ። ጅቡቲዎቹም በ1977 ዓ.ም. በተካሄደው ሪፈረንደም ነፃነታቸውን መረጡ።

ከላይ እንደተገለፀው ከኤርትራ ጋር የነበረው ፌዴራል አስተዳደርም በ1950ዎቹ ሲበረቡሩት ቆይተው በ1962 ዓ.ም ግብዓት መሬቱ እንዲፈፀም ተደረገ። ይህ ከሕግ ውጭ የሆነ የሃይል እርምጃ በ1961 ዓ.ም. Eritrean Liberation Front (ELF) እንዲፈጠርና ኢትዮጵያ ይሁን ኤርትራ በሰላሳ ዓመት ጦርነት እንዲታመሱ ምክንያት ሆነ። [1]

የአሰብ ጥያቄ በሁለት መንገድ ይነሳል። በአንድ በኩል ተቃዋሚዎች ከህዝብ ድጋፍ የሚያስገኝላቸው የፖለቲካ ጉዳይ ስለሚመስላቸው በሰፊው ያራግቡታል። በሌላ በኩል ደግሞ ከማወቅም ካለማወቅም በአንዳንድ ምሁራን ሲፃፍበት ይታያል። ቁም ነገሩ ፖለቲከኞቹ ከፖለቲካ ጥቅም አንፃር ስለሚመዝኑት ተገቢ ነው ወይስ አይደለም ብለው ብዙ ሲጨነቁበት አይታይም። አንዳንድ ምሁራን ደግሞ "ኢትዮጵያ የባህር በር ያስፈልጋታል" ከሚል አቋም ተነስተው ለመተንተን ስለሚሞክሩ ምርምሩ ከስር ወደ ድምዳሜ የሚወስድ ሳይሆን ለአቋሙ ማጠናከሪያ ምርምር መሰል ትንተና ስለሚሆን አንዱን መረጃ ወስዶ ሌላውን ወደ መተው ስለሚወስድ መጨረሻው በተሳሳተ መደምደሚያ ይቋጫል።

አቶ ገብሩ በገጽ 189 ኢህአዴግ "ኢትዮጵያን የሚጠቅመው የውል ክፍል ወደ ጉን በመተው" ይላሉ። የትኛው የውል ክፍል ነው? ጣልያን ኤርትራን ለቃ ስትሄድ "ኤርትራን ለኢትዮጵያ እንደምትመልስ ተዋውላለች" የሚለውን ይመስለኛል። ታዲያ አቶ ገብሩ ጣልያን እኮ ወዳ ኤርትራን ለቃ አልሄደችም። በሌላ ሃይል በእንግሊዞችና ተባባሪዎቻቸው ተመታ ነው እኮ የለቀቀችው። የት ሆና ነው የምትመልሰው? እንግሊዞቹ ደግሞ የራሳቸው አጀንዳ ነበራቸው። ለማንኛውም ግን የቅኝ ገዥ የትም የዓላማችን አካባቢዎች ሲገቡ የማይገቡት የመሃላ አይነት አልነበረም የመሃላዎቹ ብዛት በምሥራቅ ኤኘያ ይጠቀሙበት ከነበረው ስልት ማየት ይቻላል። አንዱ እንኳን ተፈጽሞ አያውቅም።

[1]For details, see The United Nations and The Independence of Eritrea, United Nations, 1996.

ስለዚህ ይህ የመመለሱ ጉዳይ በውሉ ሰፍሮ ከነበረ ውሉ ለጣሊያን እንጂ የጣሊያን ግዛቶችን የወረሰው የእንግሊዝ መንግሥት ይመለከተኛል ብሎ አልወሰደውም፡፡ የተባበሩት መንግሥታትም አልተቀበለውም፡፡

ሌላው የአቶ ገብሩ የአመለካከት ችግር በኤርትራ የተፈጠረው ችግር መነሻው ምንድነው የሚለው ላይ ነው፡፡ የኤርትራ ችግር የአፄ ኃይለሥላሴ ከዛም የደረግ መንግሥት የፈጠሩትና ያባባሱት በመቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ህይወት መጥፋት ምክንያት መሆኑ ላይ ነው፡፡ አቶ ገብሩም ካለፉት መንግሥታት "በጠላቶች የመከበብ" አመለካከት (siege mentality) የወጡ አይመስሉም፡፡ በእውነት ከሆነ የባሰባቸው ነው የሚመስሉት፡፡ በገፅ 474 "ዓረቦች በኢትዮጵያ ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር ያደርጉት እንቅስቃሴ ቀይ ባህርን ከማሳጣት አልፎ በሰላሟና በኢኮኖሚዋ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ስለደረሰ ችግሩን ዘላቂ በሆነ መንገድ ለመፍታት ኢትዮጵያውያን ዜጎችና መንግሥትም መንቀሳቀስ ይገባቸዋል፡፡" ይላሉ፡፡ የኤርትራ ህዝብ ትግል ዓረቦች የፈጠሩት ነው ለማለት ምንም የቀራቸው አይመስልም፡፡ አቶ ገብሩ አሁን ካምፓቸውን ለውጠው የህዝብ መብት ከሚሸራርፈው ወገን ከተሰለፉ በኋላ ለሰላሳ ዓመት መስዋእት የተከፈለበትን የህዝብ ትግል ቢያንስ የህዝብ ድምፅ ነው ብለው መቀበል ተስኖአቸዋል፡፡ ብቁ የውጭ ጉዳይ እና የደህንነት ፖሊሲ ስትራቴጂ መነሻው ከውስጥ ነው፡፡ የውስጥ ችግር ሳይኖር "የውጭ ጠላት" እጁን የሚያስገባበት ሁኔታ የለም፡፡ ለዚህ ነው የውስጣችንን ዋናው ጠላት ድህነትን ማስወገድ የሚሆነው፣ ድህነት በተቀነሰ ቁጥር የዲሞክራሲና የኢኮኖሚ ግንባታ ችግሮቻችን ትርጉም ወደ ሌላቸው ደረጃ እየወረዱ የሚሄዱት፡፡ በዚሁም ልክ ብቁና ዘመናዊ የመከላከያ ሃይል ሲታከልበት የዚች አገር መሠረታዊ ጥቅሞች ይከበራሉ፡፡ ከጐረቤቶቻችንም በጋራ ጥቅምና በመከባበር መርህ አብረን እንሰራለን፣ ኢኮኖሚያዊ ትስስራችንን እናጠናክራለን በዛው መጠን ደግሞ የእኛ ብቻ ሳይሆን የአካባቢያችንና ክፍለ አህጉራችንን ሰላም በፅኑ መሰረት እንገነባለን፡፡

እንዲያውም አሁን በአባይ ወንዝ በመግባባት፣ በጋራ ጥቅምና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ win-win የሆነ ግንኙነት እንመሰረታለን ስንል የአቶ ገብሩ ምክረ-ሃሳብ (recommendation) የሚገረም ነው፡፡ "የኢትዮጵያ በዚህ ወንዝ ላይ ቁጥጥሯን አጠናክራ፣ የሃይልና የመሣሪያ ባለቤት ሆና፣ በእነዚህ አገሮች ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር በቀይ ባህር ላይ ቁጥጥሯን የማጠናከሯ ጊዜ አሁን ነው" ይላሉ፡፡ እባክዎትን አቶ ገብሩ zero-sum game አይደለም

እየተጫወትን ያለነው፣ በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ፣ በእኩልነት ተጠቃሚነታችንን በማረጋገጥ ኢኮኖሚያችንን ደግሞ በማስተሳሰር (economic integration) ነው አብረን የምናድገው። በአውሮፓ እኮ በመቶዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት ያንዱ መጠቀም ያንዱ መጐዳት ነው ብለው ሲያስቡ የነበሩት ጀርመኖችና ፈረንሳዮች አሁን ተነጣጥለውም መተንፈስ ወደማይችሉበት ደረጀ እየደረሱ ነው። "አረ ገዳይ" ለምን አስፈለገ። ጦርነት የፖለቲካ ፍላጐት ማስቀጥያ ነው የሚለው አባባል እያረጀ አሁን ጦርነት የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ስራ መውደቅ ክስተት ነው ወደሚለው እየተሸጋገርን ነው። የመከላከያ አቅማችን ሌት ከቀን ብቃት ያለው ዘመናዊ ሃይል እንዲሆን ማድረግ አለብን ግን ከሩቅ የመከላከልና (deterence) ፍላጐትን የማስፈፀምያ የመጨረሻ ምርጫ (last resort) መሆኑ ግን በግልፅ መታወቅ አለበት።

በተደጋጋሚ አቶ ገብሩም በአሰብ ያለዎት አቋም የሚጋሩ ሰዎችም ኤርትራ "በኢትዮጵያ ከፍተኛ ተፅእኖ ፈጣሪ ናት" ስለዚህ የባህር በር ከሌለን በህልውናችን ከፍተኛ አደጋ ይኖራል የሚሉትን ዘይቤ ያራምዳሉ። ይህ አባባል ድሮም ቢሆን ትላልቅ አገሮች ትናንሽ አገሮች blackmail የሚያደርጉበት አለፍ ሲልም የሚወሩበት ሁኔታ ነበር። በሁለተኛ ዓለም ጦርነት ሶቭየት ዩኒየን የባልቲክ አገሮችን (Lithuania, Estonia and Lativia) ፊንላንድን (Finland) "አገሬን ለመከላከል አያመቸኝም" በሚል ወረራ የተካሄደበት ሁኔታ ታሪክ ያስታውሰናል። በተጨማሪም ጀርመንና ሶቭየት ህብረት ፖላንድን ለሁለት የተካፈሉበት ሂደት "ተፅእኖ የሚፈጥር ሁኔታ" አለ በሚል ነው። በቅርቡም የCrimea "ሪፈረንደም" እና ወደ ሩሲያ የመጠቃለል መነሻው ያው ነው። ስለሆነም "ተፅእኖው" አለ ከተባለም ተፅእኖውን ለመቀነስ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ትስስር መፍጠር ነው እንጂ ያንድን አገር መሬት ህዝቡም እንዳለ ሳንረሳ እንወስዳለን ማለቱ በኢንተርናሽናል ሕግ ይሁን በዲፕሎማሲ ወዘተ… የሚሉትን ቆም ብለን በትንሹ ሰላምና መረጋጋት በቀጠናው ከማስፈን አንጻር ያስኬዳል ወይ? ብለን ጠይቀን መልስ ማግኘት ይኖርብናል።

ኤርትራ ከ1993 ዓ.ም. ወዲህ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች ባሉበት ሪፈረንደም ተካሂዶ በውጤቱም መሰረት ነፃ የሆነች አገር ነች። በ28 May 1993 የፀጥታ ምክር ቤቱን የውሳኔ ሃሳብ (recommendation) ተከትሎ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት 182ኛ አባል ሃገር አድርጎ ተቀብሏታል። በየትኛውም መንገድ አንድ ሃገር የሌላውን ሃገር ያለፍቃድ መሬት መውሰድ እንደማይቻል የሚታወቅ ነገር ነው።

በፍላጐት የባህር በር ሰጠ የሚባል ሃገር ምሳሌ የሚሆን (precedence) እኔ እስከማውቀው ድረስ የለም፡፡ ስለሆነም በባህር በር አጠቃቀም ላይ ያለው ስምምነት በ1982 ዓ.ም. የፀደቀው UN Convention on the Law of the Sea ነው፡፡ ይህ ስምምነት ወደብ አልባ የሆኑትን አገሮች ወደ ባህርም ከባህርም የመጠቀም መብት ይሰጣቸዋል፡፡ Article 125 (1) "Land-locked States shall have the right of access to and from the sea for the purpose of exercising the rights provided for in this Convention including those relating to the freedom of the high seas and the common heritage of mankind. To this end, land-locked States shall enjoy freedom of transit through the territory of transit States by all means of transport."

የዚህ አንቀፅ ዋና ቁም ነገር ወደብ አልባ የሆኑ ሃገራት ከባህርም ሆነ ወደ ባህርም እንዲሁም በወቅያኖሶች ላይ የመጠቀም መብት እንዳላቸውና በሁሉም የትራንስፖርት ዓይነትና መንገድ የመገልገል መብት ይሰጣቸዋል፡፡

ይህን ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግ በአካባቢያችን ወደብ ካላቸው ሃገራት ጥቅማችንን በተሟላ በሚያስከብር መንገድ መዋዋልን ይጠይቃል፡፡ ውል ብቻ ግን በቂ አይደለም፡፡ ከእነዚህ አገሮች በጋራ ጥቅም መተሳሰር ይኖርብናል፡፡ ይህን ትስስር በቂ ትኩረት ሰጥተን ማጐልበት ይገባል፡፡

የዓለም አቀፍ ሕጉ የሚፈቅደው ይሄው ነው፡፡ ከዚህ በላይ ልውሰድ ቢባል በፍላጐት የማይሆን ህልም ነው፡፡ በሃይል ደግሞ ወረራ ይሆናል፡፡ አሁን በያዝነው ከጐረቤቶቻችን ጋር ያለው ኢኮኖሚያዊ ትስስር ጠንክረን ከቀጠልንበት ውጤቱ ትልቅ ዋስትና ይሰጠናል፡፡ ይህ ሁኔታ አሁን የተፈጠረ ሳይሆን ከቀደሙት ኋላቀር መንግሥታት የወረስነው ችግር መሆኑ መገንዘብ ያሻል፡፡ አሁን መፍትሄ ስንፈልግ ግን በሰለጠነና ዓለም ዓቀፍ ሕግን በተከተለ መሆን ይኖርበታል፡፡

አንዳንድ ፀሐፊዎች የAlgiers Agreement የባህር በር የማግኘት እድላችን እንዳጨለመብን ያቀርባሉ፡፡ ይህ የAlgiers Agreement ይዘት አለመገንዘብ ነው ወይም ለምን ወታደራዊ የበላይነት እያለን አሰብን ቆርሰን አልወሰድንም ነው የሚሆነው፡፡ በሃይል የሌላ ሉዐላዊ ሃገር ግዛት ቆርሶ ወስዶ በሰላም መተኛት እንደማይቻል የታወቀ ነው፡፡ የAlgiers Agreement ኢትዮጵያን ወደብ አልባ እንዳላደረጋት ማንም የፖለቲካ ሀሁ ያለው የሚያውቀው ነው፡፡

ታዲያ ዓላማው ምንድነው? ይህን ነገር የፖለቲካ ጥቅም (Political currency) ካለው ለመጠቀም ነው። ይህ ግን የኢትዮጵያ ህዝብ ብዙ ያየና በብዙ ችግር ያለፈ ህዝብ ስለሆነ አንድምታውን አያጣውም።

በቅርቡ አቶ ገብሩ መቐለ ባደረጉት ስብሰባ "በታሪክ፣ በሕግ የባህር በር ይገባናል ስንል ለምን አትጠይቁ ይሉናል። ለምን ሞክሩት አይሉንም?" ብለው ለተሰበሰበው ይናገሩ ነበር። በራስዎ ቢሞክሩት ችግር ያለው አይመስለኝም። እዚህ አገር ሕግን ተከትለው የፈለጉትን ማለት ይችላሉ። በሕግ እንደማያስኬድ፣ ለዚህ የሚሆን ስምምነትም የቆየ ልምድም እንደሌለ ገልጫለሁ። ምናልባት ለፖለቲካ የሚጠቅም ከሆነ ሊቀጥሉበት ይችላሉ። ፖለቲካም ቢሆን ተግባራዊ መሆን ስለሚችል ነገር እንጂ በህልም ብቻ ስለሚታይ ሃሳብ የሚሸፍን አይመስለኝም። እዚህ ላይ የጀርመኑ መሪ Otto von Bismarck አባባል ትዝ አለኝ። "Politics is the art of the possible." ፖለቲካ የሚቻለውን ነገር፣ የሚጨበጠውን ነገር ለመፈፀም የሚያገለግል ጥበብ ነው። የማይቻል ነገር ፖለቲካ አይደለም። አሁንም በማይቻለው ነገር ላይ ታች ማለቱን ሊቀጥሉ ይችላሉ። እምቃወመው ግን ለማይሆን ነገር ህዝቡን ከስራው ማስፈታት፣ በልማቱ ላይ ትኩረት ሰጥቶ (focused) ሆኖ እንዳይሰራና ውጤታማ እንዳይሆን ማዘናጋት ነው።

## 7. ማጠቃለያ፣

አቶ ገብሩ በመግቢያው እንዳነሳሁት ብዙ ጉዳዮችን አንስተው ለመገምገም ሞክረዋል። ብዙ ስህተት ያለበት መጽሐፍ ስለሆነ ሁሉንም አንስቶ ለመተቸት ሌላ ራሱን የቻለ መጽሐፍ መጻፍን ይጠይቃል። የመረጥኩት ጉላ ጉላ ያሉትን ለአሁኑ ሁኔታ እርባና ይኖራቸዋል ብዬ በገመትኳቸው ላይ የራሴን አስተያየት ለመስጠት ሞክሬአለሁ። ለዚሁ አስተያየቶቼም መነሻ የሚሆን ንድፈ ሃሳብ ወይም perspective ለማስቀመጥ ሞክሯል።

በዲሞክራሲ ግንባታ ላይ ሰፋ ያለ አስተያየት መስጠት በአሁኑ ጊዜ አስፈላጊ ይመስለኛል። በምርጫው ዋዜማ እንኳን ስናይ ሁሉም ተቃዋሚ ነኝ የሚል ስለሊብራል ዲሞክራሲ ብፁዕነት ነበር የሚሰብከው። ስለሆነም የሊበራል ዲሞክራሲ ይዘት ምን እንደሆነ፣ በኢትዮጵያ ሁኔታም ለመተግበር ቢሞከር ያለው ጉድለት ምን እንደሆነ፣ ይህን ጉድለቱን ልማታዊ ዲሞክራሲ እንዴት መሙላት እንደሚችል ተዘርዝሯል። ያደጉትና የበለፀጉት ሃገራት እነሱ ባለፉበት መንገድ በተለይም የመንግሥት ሚና ለምን ትርጉም በሌለው ደረጃ መገደብ እንደሚፈልጉ ተገልጿል። ይህ ምናልባት በሁለቱ የዲሞክራሲ ግንባታ አማራጮች ያለው ልዩነትና ለልማታችን ያላቸው አንድምታ ለመለየት ያስችላል የሚል እምነት አለኝ።

ህወሓት ሲመሰረት ከነበሩት ድርጅቶች ማለትም ከኢህአፓ፣ ከመኤሶንና ከኦነግ ከመሳሰሉት የሚለየው መሰረታዊ የሆነ የመስመሮችና ስትራተጂዎች ስህተት ያለመፈፀሙ ነው። ህወሓት መስመሮቹንና ስትራቴጂዎቹን በየጊዜው የነበረው ለውጥና እድገት በተገቢው መንገድ አንብቦና ገምግሞ በየጊዜው በማሻሻልና በማዳበር ራሱን ሁሌም ለለውጥ ዝግጁ ሆኖ በመገኘቱ ነው። እንደሚታወቀው ሌሎች ትላልቅ የተባሉትና ከፍተኛ ተስፋ የተጣለባቸው ድርጅቶች ሲንከባለሉ ህወሓት ህዝቡን በመስመሩ አሰልፎ፣ የህዝቡን ድጋፍ አግኝቶ ከሌሎቹ አጋር ድርጅቶች ጋር ተባብሮ ወደ ማይበገር ሃይል (formidable and effective force) የተለወጠው ሁሌም ለለውጥ ዝግጁ ስለነበር ነው። እዚህ ላይ Charles Darwin ያለው ነገር ያስታውሰኛል። “It is not the strongest of the species that survive, not the most intelligent, but the one most responsive to change”. እንግዲህ ዳርዊን በዚህ ዓለም ከመሞትና መጥፋት ድኖ የሚቀጥለው ፍጡር ጉልበተኛው አይደለም፣ አዋቂና ብልጣ ብልጡም አይደለም፣ በየጊዜው ለሚኖረው ለውጥ ራሱን ያዘጋጀና ለውጥን የተቀበለ ብቻ ነው ይላል። ዳርዊን ያለው ነገር መፈፀሙን ነው ያለፈው ይሁን የአሁኑ ታሪክ የሚያሳየን።

ይህ ሲባል ህወሓት ብፁዕ ነበር፣ ምንም ስህተት አልፈፀመም ለማለት አይደለም። እንኳን የትግል blue print በሌለበት፣ ባለበት ስራም ብዙ ስህተቶች እየተሰሩ ግን ከስህተቶች እየተማሩ እያስተካከሉ በርካታ ውጤታማ ሥራዎች ይሰራሉ። ህወሓትም ይህን አስቸጋሪ የትጥቅ ትግል ሲያካሂድ የተፈፀመ ስህተት አልነበረም አይደለም። የህወሓት ልዩ ተሰጥኦ ግን ስህተቱን ሳይሸፋፍንና ያለምህረት ይገመግማል፣ ችግሮቹን አንጥሮ ያወጣል፣ በወቅቱ በነበረው እይታ ደግሞ ያስተካክላል። ይህንን ሌሎች ሳያደርጉት ስለቀሩ፣ ለማድረግም ወኔ አጥተው ነው የወደቁትና የተንከባለሉት። ይህ አሰራሩና አካሄዱ ነው መሠረታዊ የመስመር፣ የስትራቴጂና ታክቲክ ስህተት ላለመፈፀም ዋስትና ሰጥቶት በአፍሪካ የትልቅ ሰራዊት ባለቤት የነበረውን ደርግ እንዲንኮታኮት ዋነኛው መቺ ሃይል ለመሆን የበቃው።

አቶ ገብሩ ይህን አስደናቂ የህዝብ ትግል ለስኬቱ የ60 ሺ ወጣቶች፣ የህይወት መስዋእትነት የጠየቀው፣ ከ100 ሺ በላይ የቆሰሉለትና አካላቸውን የተጐዱበት ትግል “መለስ ብዬ ሳየው” በሚል ዘይቤ ጥላሸት ሊቀቡት የሞከሩት። እሳቸው አመራር ሁነው “እሳት ውስጥ ግባ” እያሉ ያታገሉትና ህይወቱን መስዋእት ያደረገው ታጋይ የታገለለትና በደሙና በአጥንቱ አሁን እንደፈለጉ ማውራትና መፃፍ የሚችሉበትን መድረክ እንዲፈጠር መተኪያ የሌለውን ሃብቱን ማለትም ህይወቱን የሰጠውን አሁን ደርሰው አስተዋፅኦውን ሊያጣጥሉት ቢሞክሩ ታሪክ ይቅር የሚላቸው አይመስለኝም። የዚህ ጀግና ህዝብ ትግልና መስዋዕትነት ለአሁኑ ፖለቲካ ጥቅም (expediency) መጠቀም ነውር ነው። ዞሮ ዞሮ ሓቅን ማዛባት በመጨረሻ የመንፈስ ዕረፍት የሚሰጥ አይመስለኝም። እርግጠኛ ነኝ የድሮዎቹ “አንጃ” ጓደኞቻቸው አብዛኞቹ የሳቸውን ከመሬት የለቀቀ ዝባዝንኬ የሚቀበሉት አይመስለኝም። ለማንኛውም አቶ ገብሩ የአሁኑ አቋማቸውና የፖለቲካ መንገዳቸው የግላቸው ነው። መብታቸውም ነው። አንፀባራቂ ታሪክ ያለው የህዝብ ትግልና ድርጅት ጥላሸት መቀባት ግን ክፉኛ ዝቅ ያለ ተግባር ነው።